# አዲስ ዘመን

እናድ

ረቡዕ | 83ኛ ዓመት ቁጥር 233 ሚያዝያ 23 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









# አዲስ አበባን የሚመጥነው ልማት

**አመለወርቅ ከበደ**

**ዜና ሀተታ**

በአዲስ አበባ ዋና ዋና ጎዳናዎች የግንባታ ባለሙያዎች እዚህም እዚያ በሥራ ላይ ተጠምደዋል። የኮሪደር ልማቱ እየተፋጠነ ነው። በአዲስ አበባ ከተማ እየተካሄደ የሚገኘው የኮሪደር ልማት ከተማዋን ገጽታ ከማስዋቡ ባለፈ ለነዋሪዎቹም ምቹ አካባቢ የሚፈጥር መሆኑን ለኢፕድ አስተያየታቸውን የሰጡ የከተማዋ ነዋሪዎች ይገልጻሉ።

በአራዳ ክፍለ ከተማ ራስ መኮንን አካባቢ ነዋሪ የሆኑት ብሩክ ኃይሉ(ፕ/ር) ፤ አዲስ አበባ የተለያዩ የዓለም እና የአፍሪካ ተቋማት መቀመጫ ናት። በዲፕሎማሲውም ከኒዮርክ ቀጥሎ ሶስተኛ የዲፕሎማሲ ውክልና የተሰጣት ከተማ ስለሆነች፤ እንደስሟ አበባ ማድረግ የግድ ያስፈልጋል ነው ያሉት።

ከ38 ዓመት በላይ በራስ መኮንን አካባቢ መኖራቸውን የገለጹት ፕሮፌሰር ብሩክ፤ ሁልጊዜ በተመሳሳይ ነገር መኖር አይቻልም። ከተሞች ሁሌም እየተሻሻሉ ይሄዳሉ። ታሪካዊ ቅርሶችን ከታሪካዊ እና ከክብደታቸው አንጻር በማስቀረት መሻሻል ያሉባቸውን ነገሮች ማሻሻል አስፈልጊ መሆኑን አያጠያየቅም ይላሉ።


**አዲስ አበባን ... ወደ ገጽ 11 ዞሯል**




አቶ ካሳሁን ፎሎ

# የሠራተኛውን የሙያ ደህንነትንና ጥቅምን የሚያስከብሩ ሥራዎች ይሠራሉ

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- የዘንድሮ የሠራተኛ ቀን የሠራተኛውን የሙያ ደህንነትና ጥቅም የሚያስከብሩ ስራዎችን ለመስራት በሚያስችሉ ውይይቶች እንደሚከበር የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማህበራት ኮንፌደሬሽን አስታወቀ።

የዘንድሮው የሠራተኞች ቀን ‹‹ለሰላምና ለኑሮ ውድነት መፍትሄ እንሻለን›› በሚል መሪ ሃሳብ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ135ኛ ጊዜ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለ49ኛ ጊዜ ይከበራል።

የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማህበራት


**የሠራተኛውን ... ወደ ገጽ 11 ዞሯል**


# “መላው ሕዝብ ከተማን ጽዱና ንጹህ ለማድረግ በተጀመረው ንቅናቄ ሊሳተፍ ይገባል”

## - ብፁዕ ካርዲናል አቡነ ብርሃነኢየሱስ ሊቀጳጳሳት ዘካቶሊካውያን

**ማርቆስ በላይ**


አዲስ አበባ፡- የሀገራችን ሕዝብ ከተማን ጽዱና ንጹህ ለማድረግ በተጀመረው ንቅናቄ ሊሳተፍ ይገባል ሲሉ ብፁዕ ካርዲናል አቡነ ብርሃነኢየሱስ ሊቀጳጳሳት ዘካቶሊካውያን ገለጹ።

ብፁዕ ካርዲናል አቡነ ብርሃነኢየሱስ ሊቀጳጳሳት ዘካቶሊካውያን ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ እንደገለጹት፡- ሕዝቡ ከተማን ጽዱና ንጹህ ለማድረግ በሚደረገው ንቅናቄ ላይ ሊተባበር ይገባል።

በመንግሥት ከተማን ጽዱ ለማድረግና መጸዳጃ ቤቶችን ለመገንባት ታቅዶ እየተሠራ ነው ያሉት ብፁዕ ካርዲናል አቡነ ብርሃነኢየሱስ፤ ካቶሊካዊት ቤተ


**“መላው ሕዝብ ... ወደ ገጽ 11 ዞሯል**



# ለዓባይ ግድብ ግንባታ ከአንድ ቢሊዮን 114 ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ ተሰበሰበ

**መስከረም ሰይፋ**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ዘጠኝ ወራት ለዓባይ ግድብ ግንባታ ከአንድ ቢሊዮን 114 ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ መሰብሰቡን የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ሕዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ብሔራዊ ምክር ቤት ጽህፈት ቤት አስታወቀ።

የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ሕዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ብሄራዊ ምክር ቤት ጽህፈት ቤት የሕዝብ


**ለዓባይ ግድብ ... ወደ ገጽ 11 ዞሯል**






ዶክተር ኢንጂነር ሀብታሙ ኢተፋ

# ኢትዮጵያ ከጎረቤት ሀገራት ጋር የሃይል ትስስር በመፍጠር የመሪነት ሚና እየተጫወተች ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ከጎረቤት ሀገራት ጋር የሃይል ትስስር በመፍጠር የመሪነት ሚና እየተጫወተች ነው ሲሉ የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትሩ ገለጹ፡፡

ሚኒስትሩ ዶክተር ኢንጂነር ሀብታሙ ኢተፋ በቅርቡ በአቡዳቢ እ.አ.አ በተካሄደው ወርልድ ፊውቸር ኢነርጂ ሰሚት (world Future Energy Summit) የጎንዮሽ መድረክ ላይ በመገኘት ባደረጉት ገለጻ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ ከጎረቤት ሀገራት ጋር የሃይል ትስስር በመፍጠር የመሪነት ሚና እየተጫወተች መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የፓንአፍሪካዊ ትብብር ሚና የታዳሽ ሃይል ልማትን ማሳለጥና የኢነርጂ ዋስትናን ማረጋገጥ ዋነኛ ዓላማው አድርጎ በተካሄደው መድረክ ላይ ሚኒስትሩ ቀጣናዊ የሃይል ትስስር መሠረት የመጣልና የማጠናከር ጉዳዮች ኢትዮጵያ በቀጣናው ለትብብርና ቅንጅት የሰጠችውን ትኩረት የሚያሳይ እንደሆነ ገልጸው፤ እንደተጨማሪ ማሳያም ሱዳናውያን የገጠማቸው ውስጣዊ ችግር ክፍያ እንዲፈጽሙ ባያስችላቸውም የሃይል አቅርቦት መቀጠሉን ተናግረዋል፡፡

ክቡር ሚኒስትሩ አክለውም ኢትዮጵያ ከልማት አጋሮች ጋር በመሆን የምስራቅ አፍሪካ ፓወር ፑል ለማጠናከርና ለማስቀጠል አይነተኛ ሚና እየተጫወተች ነው ያሉ ሲሆን፤ የሃይል መስመሮች መንገዶችና የቴሌኮም ኔትወርኮችን የመሳሰሉ መሠረተ ልማቶች ወደ ጎረቤት ሀገራት ተዘርግተው እንደሚገኙ ገልጸዋል።

በአጭር፣ በመካከለኛና በረጅም ጊዜ ብሔራዊ እቅድ ቀጣናዊ ቅንጅታዊ ስትራቴጂ መካተቱንና በአህጉር ደረጃ ማሳደግ ታሳቢ መደረጉን አንስተው፤ እንደሀገር ያለን የሃይድሮፓወር እምቅ አቅምና የማልማት ልምድ፤ እንዲሁም በሃይድሮ ፓወር ልማት የረጅም ጊዜ ልምድ ያለው ተቋም መገንባት መቻሉ፤ የምስራቅ አፍሪካ የአረንጓዴ ኢነርጂ ማእከል ለመሆን እንድንሠራ አስችሎናል ብለዋል፡፡

የመንግሥትና የግሉ ዘርፍ አጋርነት በመተግበር የግሉን ዘርፍ በሃይል ልማት ዘርፍ ለማሳተፍ ያለው ቁርጠኝነት አንዱ ማሳያ መሆኑን ያነሱት ክቡር ሚኒስትሩ፤ የኢትዮጵያን አሕጉራዊ የሃይል ሲስተም ማስተርፕላን መሠረት በማድረግ ለሶስት ጎረቤት ሀገራት የሃይል ትስስር መፈጠሩንና ሌሎች ሀገራትን በማካተት ወደ አሕጉራዊ ትስስር ለማሳደግ እየተሠራ ነው ብለዋል።

የሃይል መሠረተ ልማት ግንባታና ዝርጋታ ከፍተኛ መዋእለንዋይ የሚጠይቅ በመሆኑ የልማት አጋሮች ቁርጠኝነት እጅግ አስፈላጊ መሆኑን አስታውሰው፤ ኢትዮጵያ ውስጥ በሃይል ልማት ኢንቨስትመንት መሰማራት በቀጣናው የሥራ እድል ፈጠራ እና የሰላምና የጸጥታ ጉዳች ላይ አስተዋጽኦ ማድረግ ነው ብለዋል፡፡

# ሩህሩህ ልብ የሚሹ ድጋፍ ፈላጊዎች

**ማሕሌት ብዙነህ**

በጎነት በራስ ተነሳሽነት በሚመነጭ ሰብዓዊ ስሜት ከራስ አልፎ ለሌሎች መኖር ነው፡፡ ይህም የበጎነት ተግባር መስፈርቱ የመልካም ልብ ባለቤት መሆን ሲሆን ያለምንም ተለዋጭ ነገር ካለን ገንዘብ፣ ጉልበት፣ እውቀትና ጊዜ ለሌሎች መስጠትና ማካፈል ነው፡፡

በዚህ የመልካምነት መገለጫ በሆነው በጎ ፍቃድ አገልግሎትም በሀገር አቀፍ ደረጃ የበጋ እና የክረምት የበጎፍቃድ ንቅናቄ መርሀግብር በማካሄድ የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎችን ጨምሮ ተሳታፊ ሲሆኑ በዚህም በርካታ ዜጎች ተጠቃሚ መሆን ችለዋል፡፡

በሀገር አቀፍ ደረጃ ከሚስተዋለው የበጎፍቃድ አገልግሎት ባለፈ ዋና ዓላማቸው ሰውን መርዳት ያደረጉ የበጎ አድራጎት ማህበራት የሚጠቀሱ ሲሆን ማህበራቱ በተወሰነ መልኩ የእርዳታ ሰጪዎች ቁጥር መቀዛቀዙን ይናገራሉ፡፡



አቶ በላይ ንጉሴ



ወይዘሮ ሙዳይ ምትኩ

የሙዳይ በጎ አድራጎት ማህበር መስራችና ሥራ አስኪያጅ ወይዘሮ ሙዳይ ምትኩ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በሀገሪቱ ባለው ነባራዊ ሁኔታ ምክንያት ርዳታ ፈላጊ በብዛት እየጨመረ ሲሆን ርዳታ ሰጪዎች ቁጥር በተቃራኒው እየተቀዛቀዘ ነው፡፡

ከ20 ዓመታት በፊት ለ19 ልጆች በነጻ ትምህርት በመስጠት እንዲሁም ልመና ላይ ለነበሩ ሃያ አንድ ሴቶች የሥራ እድል በመፍጠር የተጀመረው ይህ የሙዳይ በጎ አድራጎት ማህበር፤ አሁን ላይ ለ650 ህጻናት እና ለ450 እናቶች የመጠለያ ፣የምግብ እና የአልባሳት ድጋፍ እያደረገ ይገኛል፡፡

በተጨማሪም እስካሁን ሁለት ሺህ ለሚሆኑ ሴቶች በተለያየ ዘርፍ ሙያ እንዲሰለጥኑ በማድረግ የሥራ እድል በመፍጠር የራሳቸውን ገቢ እንዲያገኙ ማድረግ የተቻለ መሆኑን ወይዘሮ ሙዳይ አስታውቀዋል፡፡

ማህበሩ በሥልጠና ከሚያበቃቸው እናቶች የሚሠሩ የተለያዩ የእጅ ሥራዎችን ለገበያ በማቅረብ እንዲሁም እንጀራ ምርትን በመሸጥና ወደውጭ ሀገራት ኤክስፖርት በማድረግ የራሱን ገቢ የሚያገኝ ቢሆንም፤ ለቤት ኪራይ እንዲሁም ለተለያዩ ወጪዎች ይገኝ የነበረ ርዳታ መቀዛቀዙን ተናግረዋል፡፡

ወይዘሮ ሙዳይ በተለይም ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በሀገሪቱ ባሉ የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ክስተቶች ምክንያቶች ብዙ ሰው ርዳታ ፈላጊ ነው፡፡ ነገር ግን ከግለሰቦች ብሎም ከለጋሽ ማህበራት በኩል ይገኝ የነበረው ርዳታ እና ማህበሩን ይጎበኝ የነበረው ሰው ቁጥር በጣም ተቀዛቅዟል ብለዋል፡፡

በተለይም ገንዘብ ስለለሌኝ ማገዝና መርዳት አልችልም በሚል የተሳሳተ እሳቤ ምክንያት የጎብኚዎች ቁጥር ቀንሷል ያሉት ወይዘሮ ሙዳይ፤ አንድ ሰው በገንዘብ ብቻ ሳይሆን ጸሎት ከማድረግ ጀምሮ የተለያዩ ሃሳቦችን በማቅረብ መርዳትና መጎብኘት የሚቻል መሆኑን ተናግረዋል፡፡

እንዲሁም በአብዛኛው ሰው በዓላትን ጠብቆ የሚለግስ መሆኑንም ተናግረው፤ የበጎ አድራጎት ተግባር በማንኛውም ጊዜ የሚተገበር በመሆኑ ተሳታፊ መሆን አለባቸው ብለዋል፡፡

በመሆኑም በየትኛውም የኢኮኖሚ ደረጃ የሚገኝ የማህበረሰብ ክፍል ጊዜን፣ እውቀትን እና ገንዘብን ለሌሎች በማካፈል በዚህ በበጎነት ተግባር ላይ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ጥሪያቸውን አቅርበዋል፡፡

ትኩረቱን ልጆችን ለፍሬ ማብቃት ላይ ያደረገው የአስካል በጎ አድራጎት ማህበር መስራችና ሥራ አስኪያጅ አቶ በላይ ንጉሤ በበኩላቸው፤ ማህበሩ በተለይም ሀገር በቀል ድርጅቶች እና ለጋሶችን መሠረት አድርጎ የተመሠረተ በመሆኑ የርዳታው መቀዛቀዝ ማህበሩን ለመቀጠል ከባድ አድርጎታል ብለዋል፡፡

አሁን ላይ የርዳታ ሰጪዎች ቁጥር እየተቀዛቀዘ ሲሆን ለዚህም በሀገሪቱ ያለው የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ጫናዎች ምክንያት እንደሚሆን አቶ በላይ ተናግረዋል፡፡

ይህም በተለይም ለጋሶችን መሠረት አድርጎ የተመሠረቱ ማህበራት ላይ ከፍተኛ ጫኛ እና ችግር የሚያጋላጥ ሲሆን እንደድርጅት ማህበሩን ለማስቀጠል ከርዳታ ተቋማት ከመጠበቅ በማህበሩ ያለውን የሰው ሃይል በመጠቀም እየሠሩ መሆኑንም አብራርተዋል፡፡

ሀገር ተረካቢ ልጆችን በትምህርት በማብቃት ሀገርን ማሳደግ ይገባል የሚለው የማህበሩ መስራች፤ ሁሉም ማህበረሰብ ከገንዘብ ባለፈ እውቀትንና ጊዜን ባለው አቅም ማካፈል ቢቻል የበጎ አድራጎት ማህበራትን ህልውና ማዳን እንደሚቻልም ተናግረዋል፡፡

ይህ የበጎ አድራጎች ተግባር ከራስ ቀንሶ ለሌሎች የሚሰጥ በመሆኑ ህብረተሰቡ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በችግር ውስጥ የሚገኙ ሕጻናት፣ ሴቶችን እና እናቶችን በማሰብ የመስጠትና የማካፈል ባህላችንን አጎልብተን እንቀጥል ሲሉ መልእክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

የአስካል በጎ አድራጎት ማህበር በ2011 ዓ.ም የተመሰረተ ሲሆን ችግር ላይ ያሉ ህጻናት ባሉበት ሁነው በትምህርት አቅርቦት እና በጤና ላይ አስፈላጎውን ድጋፍ እንዲያገኙ የማድረግ ሥራን የሚሰራ የበጎ አድራጎት ማህበር ነው፡፡ እስካሁንም ማህበሩ ስድስት መቶ ለሚደርሱ ህጻናት በትምህርት እና በጤና በኩል የሚያስፈልጋቸውን አገልግሎት ማሟላት እንደተቻለ አቶ በላይ አስታውቀዋል፡፡

# የበዓል ገበያውን በሚያውኩ አካላት ላይ ርምጃ ይወሰዳል

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**







አዲስ አበባ፡- በትንሳኤ የበዓል ገበያዎች ፍትህዊ የግብይት ሥርዓት እንዲኖር ገበያውን በሚያውኩ ላይ ቁጥጥር በማድረግ ርምጃ እንደሚወስድ የአዲስ አበባ ከተማ ሠላምና ጸጥታ አስተዳደር ቢሮ አስታወቀ።

የቢሮው ኃላፊ ወይዘሮ ሊድያ ግርማ ለበዓሉ ከተቋቋመው የጋራ ግብረ ኃይል ጋር ትናንት ባደረጉት ውይይት እንደተናገሩት፤ የበዓል ገበያን ከለላ በማደረግ የሚከናወኑ በርካታ ሕገ ወጥ ተግባራት አሉ። ከእነዚህም መካከል ምርትን በሕገ ወጥ መንገድ በማከማቸት ሰው ሰራሽ የምርት እጥረት መፍጠርና ለበዓል የሚቀርቡ ምርቶች ላይ በዓድ ነገር መቀላቀል ይገኙበታል።

በተለይ የቁም እንስሳት መገበያያ ማእከላት ደላሎች የራሳቸውን ዋጋ በማውጣት ገበያውን የማውክ ሥራ ይሠራሉ። እንዲሁም አርሶ አደሮችም በስፋት ምርት ይዘው ወደገበያ ስለሚመጡ የሀሰተኛ ገንዘብ ዝውውር ይኖራል ያሉት ኃላፊዋ፤ በዘንድሮውም የትንሳኤ በዓል ይህንን አጠናክሮ በመቀጠል የኑሮ ውድነትን በመቆጣጠር የተረጋጋ ገበያ ለመፍጠር እንደሚሠራ ተናግረዋል።

የማህበረሰቡን ደህንነት ለማስጠበቅ በስፋት አስፈላጊው የቁጥጥርና ክትትል ሥራ የሚከናወን መሆኑን ገልጸው፤ በእነዚህ ተግባራት ለይ ተሰማርቶ የሚገኝ ካለ በሕግ አግባብ ተገቢው ርምጃ እንደሚወሰድበት አመልክተዋል።

የገበያ መረጋጋት እንዲኖር ምርቶች ወደ ከተማ ሲገቡ ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑን ጠቁመው፤ ከተማ ከገባ በኋላም በአግባቡ ለማህበረሰቡ ተደራሽ መሆኑ ላይ ክትትል እንደሚደረግም ተናግረዋል።

እንደ ቢሮ ኃላፊዋ ገለጻ፤ ግብረ ኃይሉ በአምስቱም በሮች እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱ አለአግባብ ምርት ይከማችባቸዋል ተብሎ የሚታሰቡ መጋዘኖችና ቦታዎች ላይ ቁጥጥር ያደርጋል። የማህበረሰቡን ሰላም በሚያውክ መልኩ በጎዳና ላይ የሚደረጉ የቁም እንስሳት ንግድና ለጤና ጠንቅ በሆነ መልኩ በየመንደሩ የሚፈጸም የእንስሳት እርድ ላይም ቁጥጥር የሚካሄድ ይሆናል።

ለዚህም ከሸገር ከተማ አስተዳደር፤ ከደንብ ማስከበር ቢሮ፤ ምግብና መድሃኒት ቁጥጥር ባለሥልጣን፤ ፖሊስና ሌሎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት እንደሚሠራም ጠቁመዋል ።

እነዚህ የቁጥጥር ሥራዎች ማህበረሰቡን ከዋጋ ንረት ከመቆጣጠር ባለፈ ከበዓል የገበያ ግብይት መንግሥት ተገቢውን ገቢ ለመሠብሠብ የሚያስችል እንደሚሆነ አመልክተው፤ በበዓላት ወቅት ወንጀለኞች የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም በስፋት ለስርቆትና ለዝርፊያ የሚንቀሳቀሱ በመሆኑም የሕብረተሠቡን ደህንነት ለማስጠበቅ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር እንደሚደረግም ተናግረዋል።

ዜና



አቶ ጥበቡ ታደሰ

## ኮሚሽኑ ከ14ሺ በላይ በአጀንዳ ማሰባሰብ ሂደት የሚሳተፉ ተወካዮችን አስመርጧል

መዓዛ ማሞ

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን እስከአሁን ከ14ሺ በላይ በአጀንዳ ማሰባሰብ ሂደት የሚሳተፉ ተወካዮችን ማስመረጡን ገለጸ፡፡

የምክክር ኮሚሽኑ ቃል አቀባይ አቶ ጥበቡ ታደሰ ኮሚሽኑ ባከናወናቸው እና በቀጣይ በሚያከናውናቸው ተግባራት ላይ ትናንት በሰጡት መግለጫ እንደገለጹት ከ940 በላይ በሚሆኑ ወረዳዎች የተሳታፊዎች ልየታና በአጀንዳ ግብዓት ማሰባሰቢያ ሕዝባዊ መድረኮች ላይ የሚሳተፉ ተወካዮችን የማስመረጡ ተግባር ሲሠራ ቆይቷል፡፡

850 በሚሆኑ ወረዳዎች ላይ ሥራው ሙሉ ለሙሉ መጠናቀቁን ገልጸው፣ በሂደቱ 130ሺህ የሚሆኑ ዜጎች ተሳትፈው ከ14ሺህ በላይ ተወካዮች መመረጣቸውን ተናግረዋል፡፡

አፋር፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ አዲስ አበባ፣ ጋምቤላ፣ ድሬዳዋ፣ ሀረሪ፣ ሲዳማ፣ ደቡብ ምዕራብ፣ ደቡብ እና ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልሎች የተወካዮች መረጣ ሙሉ ለሙሉ የተከናወነባቸው ሲሆኑ በሶማሌ ክልል 25 የሚሆኑ እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል ከ70 በማይበልጡ ወረዳዎች የማጠናቀቂያ ሥራዎች እንደሚቀሩ አመላክተዋል፡፡

ይህ በክልል፣ በድሬዳዋና አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እንዲሁ በፌዴራል ተቋማት የሚወከሉትን እንደማይጨምር የተናገሩት ቃል አቀባዩ፤ በዚህ ደረጃ ያሉ ተሳታፊዎች ሲጨመሩ በአጀንዳ ግብዓት ማሰባሰቢያ መድረኮች የሚሳተፉ ተሳታፊዎች ቁጥር እንደሚጨምር ጠቁመዋል፡፡

በቀሩት ወረዳዎች የሚደረገው ልየታ ሲጠናቀቅ ከአጠቃላይ ስራው ከ70 እስከ 75 በመቶ ያህሉን የሚሸፍን እንደሆነ ተናግረው፤ ቀሪው ከ 25 እስከ 30 በመቶ የሚሆነው የተሳታፊ ልየታ ሥራዎች ባልተጀመረባቸው የአማራ እና የትግራይ ክልሎች የሚከናወን ሥራ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

እንደ አቶ ጥበቡ ገለጻ ፤ አጀንዳ የማሰባሰብ ሂደቱን ለማስጀመር ቅድመ ዝግጅቶች እየተጠናቀቁ ነው፡፡ በክልል ደረጃ የአጀንዳ ማሰባሰቢያ መድረኮች በርካታ ቁጥር ያላቸው ተሳታፊዎች የሚስተናገዱባቸው በመሆናቸው በሰው ኃይል፣ በሎጂስቲክ እና በሌሎች ዝግጅት ማድረግ በሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ላይ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ተናግረው፤ የአጀንዳ ማሰባሰቢያ መድረኮቹ ከ8 እስከ 10 ቀናት ሊወስዱ ይችላሉ ብለዋል፡፡

በመድረኮቹ የአጀንዳ ግብዓት ከማሰባሰብ በተጨማሪ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለሚደረገው ሀገራዊ ምክክር የሚሳተፉ ተወካዮች ይመረጣሉ፡፡ በአጀንዳ የመሰብሰቢያ መድረክ እንዲሳተፉ ከተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች የተመረጡ ተወካዮች አስቀድመው ከየማህበረሰቦቻቸው ጋር በመወያየት የአጀንዳ ግብዓቶችን የማሰባሰብ ሥራ እንዲያከናውኑ ቃል አቀባዩ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

የሚዲያ ተቋማት ስለ ኮሚሽኑ የሥራ እንቅስቃሴዎች ግንዛቤ ለመፍጠርና መረጃዎችን ተደራሽ ለማድረግ እያደረጉ ላለው ከፍተኛ ጥረት ምስጋና ያቀረቡት ቃል አቀባዩ፣ በቀጣይም ይህንን አጠናክረው እንዲቀጥሉ ጠይቀዋል፡፡

# ሕገ ወጥ የእንስሳት እርድን ለመከላከል ሕብረተሰቡ እንዲተባበር ጥሪ ቀረበ

## - ድርጅቱ ለመጪው የፋሲካ በዓል ከ7 ሺህ 500 እስከ 8 ሺህ እርድ ለማካሄድ አቅዷል

ዘላለም ግዛው



አዲስ አበባ፡- ሕገ ወጥ የእንስሳት እርድ ሲፈጸምና ፍቃድ ባልተሰጠው ተሽከርካሪ ዝውውር ሲከናወን ከተመለከተ ጥቆማ በማቅረብ ሕገ ወጥ ድርጊቱን ለመከላከል እና ለማስቆም ሕብረተሰቡ ተባባሪ እንዲሆን የአዲስ አበባ ቄራዎች ድርጅት አሳሰቧል፡፡ ለመጪ ፋሲካ በዓል ከ7 ሺህ 500 እስከ 8 ሺህ እርድ ለማካሄድ ማቀዱን አስታውቋል

የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጁ አቶ ሰይድ እንድሪስ የትንሳኤ በዓልን በማስመልከት ትናንት በሰጡት መግለጫ፤ ህብረተሰቡ ስጋ አቅራቢዎች ሕጋዊ የእንስሳት እርድ ፍቃድ የተሰጣቸው እና የተመረመረ ስጋ አቅራቢ መሆናቸውን አጣርቶ ገዝቶ ሊጠቀም እንደሚገባ መክረዋል፡፡

ለንግድ የሚቀርብ ሕገ ወጥ የእንስሳት እርድ እና ዝውውር ከሕብረተሰቡ የተደበቀ ባለመሆኑ ሕብረተሰቡ ድርጊቱን ለመከላከል በሚደረግ ሂደት ለሕግ አካላት ጥቆማ በማቅረብ ተባባሪ መሆን እንዳለበትም ነው የተናገሩት፡፡

ከወትሮው በተለየ መልኩ እንስሳቶች እርድ ለማከናወን በቂ ዝግጅት መደረጉን አመልክተዋል፡፡

ድርጅቱ የከብት ስጋ የፍየል እና የበግ ስጋ በተመጣጣኝ ዋጋ እንደሚሸጥም ተናግረዋል፡፡

ከፍተኛ መጠን ያለውን እርድ ለማከናወን ዝግጅት መደረጉን በመጠቆምም፤ ድርጅቱ ከ7 ሺህ 500 እስከ 8 ሺህ እርድ ለማካሄድ በማቀድ ተጨማሪ የሰው ሃይል በመጨመር ቅድመ ዝግጅቱን ማጠናቀቁንም ተናግረዋል።

መደበኛ የዕርድ አገልግሎት ዋጋ ለዳልጋ ከብት አንድ ሺህ 400 ሲሆን በልዩ ሁኔታ ደግሞ አንድ ሺህ 700 ብር መሆኑን እንዲሁም ለፍየል እና ለበግ የአገልግሎት ዋጋ 167 ብር፣ በልዩ ሁኔታ ደግሞ 230 ብር እንደሚያስከፍል አመልክተዋል፡፡

በሕገ ወጥ የእንስሳት ንግድ ጋር ተያይዞ ከግብር እና መሰል የታክስ ስወራ ከተማ አስተዳደሩ አንድ ነጥብ 35 ቢሊዮን ብር እንደሚያጣ ነው ያመለከቱት፡፡

ከጾም በፊት በሉካንዳ ቤቶች በተደረገ ድንገተኛ ፍተሻ ሕገ ወጥ ተግባር ላይ ተሰማርተው የተገኙ 85 ቤቶች እንዲታሸጉ መደረጉን ጠቁመው፣ በቀጣይ ሕገወጥ እርድን ለመከላከል የተጠናከረ ርምጃ እንዲሚወሰድም ነው የገለፁት፡፡

ሕገ ወጥ እንስሳት እርድ ተፈጽሞ ሲገኝ ስጋውን መውረስ እና ማስወገድ ሲተገበር እንደነበር በማስታወስም፤ በቀጣይ በሁሉም ማህበራዊ የግንኙነት አውታሮች ሕገ ወጥ እርድ የሚፈጽሙና የሚሸጡ አካላትን ለህብረተሰቡ የማሳወቅ ሥራ ይከናወናል ብለዋል፡፡

በሕጋዊ መልኩ ፍቃድ አውጥተው በሕገ ወጥ ንግድ የሚንቀሳቀሱትን አካላት የንግድ ፍቃዳቸውን እንዲሰረዝ የሚደረግበት አሠራር መዘርጋቱንም ጠቁመዋል፡፡

ሕገ ወጥ እንስሳት እርድ የተስፋፋው ከግንዛቤ ችግር፣ ቄራዎች ተደራሽ ካለመሆናቸው እና ለግብር ስወራ ታስቦ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ድርጊቱን የሚፈጽሙና የሚያስፈጽሙትን ከፍትህ ቢሮ ጋር በመነጋገር በሕግ እንዲጠየቁ የሚደረግበት ሥራ ይሠራል ያሉት ሥራ አስኪያጁ፤ ሕገ ወጥ ስጋ የሚያዘዋውሩ ተሽከርካሪዎች እንዲወረሱ ለሚመለከተው አካል ጥቆማ በማቅረብ ድርጊቱን የመከላከል ሥራ እንደሚሠራም ተናግረዋል፡፡

የአዲስ አበባ ልኳንዳ ነጋዴዎች ማህበር ሥራ አስኪያጅ አቶ አየለ ሳህሌ በበኩላቸው፤ ህብረተሰቡ ሕጋዊ የእርድ ፍቃድ አገልግሎት ከተሰጣቸው አካላት በመጠቀም ጥራቱና ደህንነቱ የተጠበቀ አገልግሎት ማግኘት እንዳለበት መክረዋል፡፡ ማህበሩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ሕገ ወጥ እርድ የሚፈጽሙ አካላትን ለመከላል እንደሚሠራም ነው የገለፁት፡፡

# ሚኒስቴሩ ፕሮጀክቶችን በተያዘላቸው ጊዜ እንዲያጠናቅቅ ምክር ቤቱ አሳሰበ

ማኅሌት ብዙነህ



አዲስ አበባ፡- የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር የሚያከናውናቸው የመስኖ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ለማጠናቅ በትኩረት ሊሠራ ይገባል ሲል የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አሳሰበ።

የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ትናንት ባካሄደው 23ኛ መደበኛ ስብሰባው የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴርን የ2016 በጀት ዓመት የ 9 ወራት የዕቅድ አፈፃጸም ገምግሟል።

የውሃ፣ መስኖ፣ ቆላማ አካባቢና የአካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ፈቲያ የሱፍ እንደገለፁት፤ ሚኒስቴሩ የሚያከናውናቸውን ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ጊዜ የማጠናቀቅና የአፈጻጸም ክፍተት አለበት፡፡

እንዲሁም በክልሎች መካከል የአፈፃፀም ልዩነቶች፤ የጥናትና ዲዛይን ሥራ ዝቅተኛ መሆን፤ ግንባታ ጥራት ማነስ የሚታዩ ክፍተቶች መሆናቸውን ጠቅሰው፤ ይህም ለጊዜ እና ለሀብት ብክነት የሚዳርግ መሆኑን ተናግረዋል።

የፕሮጀክቶች መዘግየት ብድርን ከመመለስ አንጻር ክፍተት የሚፈጥር እና የሕዝብ የልማት ጥያቄ ከመመለስ አንጻር ችግር የሚፈጥር መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

ሚኒስቴሩ በጥናትና ዲዛይን የያዛቸው ከሦስት ዓመት እስከ 11 ዓመት ያስቆጠሩ 27 ፕሮጀክቶች መኖራቸውን በማሳያነት ጠቅሰዋል፡፡

ከ27ቱ ፕሮጀክቶች 10 የሚሆኑት ላይ በዘጠኝ ወራት ውስጥ የተከናወነ ሥራ አለመኖሩን ተናግረው፤ በተጨማሪም አንድ ፕሮጀክት የተቋረጠ መሆኑን አመላክተዋል፡፡

መሠረተ ልማት ግንባታን በተመለከተም ካሉት 28 የመስኖ መሠረተ ልማቶች 19 የሚሆኑት በዘጠኝ ወራት ውስጥ ምንም ሥራ ያልተከናወነባቸው መሆናቸውን አብራርተዋል፡፡

በተጨማሪም የአርብቶ አደር ማህበረሰቡን ከድርቅና ከጎርፍ የመሳሰሉት አደጋዎች ለመከላከልና ሕይወት ከማሻሻል አንጻር በቅንጅት ከተቋማት ጋር የመሥራት ክፍተት፣ እቅድና ሪፖርት ከመሬት ጋር ካለው ሥራ ያለመናበብ፣ ችግር አፈታት ክፍተት የሚስተዋል ሲሆን በልዩ ሁኔታ ታይቶ መፈታት አለበት ብለዋል፡፡

በመሆኑም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የተጀመሩ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ጊዜ ለማጠናቀቅ በትኩረት ሊሠራ እንደሚገባ ተመላክቷል።

የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር ኢንጂነር አይሻ መሀመድ በሰጡት ማብራሪያ እንደገለፁት፤ ለፕሮጀክቶች መዘግየት ትልቁን ድርሻ የሚይዘው የዲዛይን ችግር ነው። ይህም በበርካታ ፕሮጀክቶች ከ75 በመቶ የሚሆነውን የጊዜ መጓተት እና የገንዘብ መጨመር ድርሻ ይወስዳል፡፡

በክትትል ያልተሠራ ዲዛይንና አዋጭነቱ በትክክል ያልታወቀ ፕሮጀክት እንዲሁም በአካባቢው ላይ የሚኖረው ተጽእኖ በአግባቡ ባለመሠራቱ ምክንያት ፕሮጀክቶቹን ለማጠናቀቅ አዳጋች ያደርገዋል ሲሉም አብራርተዋል፡፡

እንዲሁም የአዋጭነት ጥናት በትክክል አለመጠናት፣ በአንዳንድ አካባቢዎች ያለው የፀጥታ ችግር፣ የወሰን ማስከበርና የካሳ ክፍያ ጉዳዮች፣ የሥራ ተቋራጭ አቅም ውስንነት እና በዘርፉ የአሠራር ስታንዳርድ አለመኖር እንዲሁም የግንባታ ግብዓቶች እጥረትንና የዋጋ መናር ተጠቃሽ ችግሮች መሆናቸውን አስረድተዋል።

በክልሎች መካከል የሚስተዋለውን የአቅም ልዩነትን ለማጥበብ ለክልሎቹ የአፈጻጸም አቅምን ለማሳገድ የተለያዩ ሥልጠና እና ልምድ ልውውጥ የሚያካሂድ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በመሆኑም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ያሉበትን ችግሮች በመፍታት ሀገሪቱ ያላትን የመስኖ አለኝታዎች እና የቆላማ አካባቢ ሀብቶችን በማልማት ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ የዜጎችን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተጠቃሚ ለማድረግ ይሠራል ብለዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ለኢንዱስትሪው ዕድገት የዘርፉ ተዋንያን ከፍ ባለ የኃላፊነት መንፈስ ሊንቀሳቀሱ ይገባል!

ሀገራችን ወደ ኢንዱስትሪ ለምታደርገው ሽግግር ስኬታማነት መንግሥትን ጨምሮ የባለሀብቶች እና የሌሎች የዘርፉ ተዋንያን ንቁ ተሳትፎ ወሳኝ ነው። በተለይም ዘርፉን በሚፈለገው መልኩ ውጤታማ በማድረግ ሂደት ውስጥ መንግሥት ዘመኑን የሚዋጁ ፖሊሲዎችን በመቅረጽ ለውጤታማነታቸው በቁርጠኝነት መንቀሳቀስ ይጠበቅበታል።

የኢንዱስትሪ ዘርፍ በ1930 ዓ.ም መጀመሪያ አንስቶ እንደ ሀገር ማቆጥቆጥ እንደ ጀመረ ፣ በዚህም ከስምንት አስር ዓመታታት በላይ እድሜ እንዳስቆጠረ የታሪክ መዛግብት ይናገራሉ። በአብዛኛው በውጭ ባለሀብቶች የተጀመረው የዘርፉ እንቅስቃሴ በሂደት ፣ በመንግሥት እና በግል ባለሀብቶች ተሳትፎ እመርታ ያሳየበትም ሁኔታ ተፈጥሯል።

የእንዱስትሪው ዘርፍ በአግባቡ መሬት ባልረገጠበት ሁኔታ ፣ በ1960ዎች በሀገሪቱ የተጀመረው የለውጥ እንቅስቃሴ ፣ እነዚህን ኢንዱስትሪዎች በመውረስ አጠቃላይ በሆነው በዘርፉ ዕድገት ላይ ከፍ ያለ ተጽዕኖ ፈጥሯል። “በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ” እንደሚባለው አብዮቱን ተከትሎ የተፈጠሩ የርስ በርስ ጦርነቶች ዘርፉን የበለጠ አዳክመውታል ።

የ1983 ዓ/ም ሀገራዊ ለውጥም ቢሆን፣ ለዘርፉ ተገቢውን ትኩረት የሰጠ አልነበረም። እንዲያውም በፕራይቬታይዜሽን ስም የተደረገው የመንግሥት ፋብሪካዎችን ወደ ግል የማዘዋወር እንቅስቃሴ በብዙ ችግሮች መሞላቱ ፣ ለዘርፉ ዕድገት ተጨማሪ ፈተና በመሆን በዓለም አቀፍ ጫና ሳይቀር በፖሊሲ ደረጃ የተወሰዱ ርምጃዎች ውጤታማ ሳይሆኑ ቀርተዋል።

ይህ ሀገራዊ እውነታ በኢንዱስትሪው ዘርፍ ላይ ጥቁር ጠባሳ በመጣል ፣ የውጭ ባለሀብቶችን ጨምሮ ዜጎች በዘርፉ ሀብታቸውን አፍስሰው ተጠቃሚ የሚሆኑበትን የቀደመ መነሳሳት አቀዝቅዟል። ከዚያም ባለፈ በዘርፉ ተሰማርተው የሚኖሩ ባለሙያዎች /ወዝአደሮች/ ባላቸው እውቀት እና ክህሎት ተወዳዳሪ ሆነው ተጠቃሚ የሚሆኑበትን አማራጭ አቀጭጮባቸዋል።

ሀገሪቱ ለኢንዱስትሪዎች መስፋፋት የሚሆን ከፍተኛ የተፈጥሮ ሀብት እና የሰው ኃይል ቢኖራትን ይህን ሀብት አልምቶ መጠቀም ፣ የሚያስችል አቅም እና የተመቻቸ ፖሊሲ አለመኖሩ ለዘርፉ እድገት ትልቅ ተግዳሮት ሆነው ቆይተዋል። ችግሩን በዘርፉ የተሠማሩ ዜጎችን ሕይወት በብዙ ተፈታትኗል ።

ከ2010 ሀገራዊ ለውጥ ማግስት ይህንን ሀገራዊ ችግር ለመፍታት ሰፊ ጥረቶች ተደርገዋል። በወቅቱ በዘርፉ የተጀመሩ ውጭ እና የሀገር ውስጥ ኢንቨስትመንቶች የበለጠ ተጠናክረው የሚቀጥሉበትን የፖሊሲ አቅጣጫ ከመቅረጽ አንስቶ ፣ የኢንዱስትሪው ዘርፍ በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ውስጥ የጎላ ስፍራ እንዲኖረው ለማስቻል በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል።

በዚህም የኢንዱስትሪው ዘርፍ ሀገሪቱ ተግባራዊ እያደረገችው ባለው ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ፖሊሲ ውስጥ ትኩረት ከተሰጣቸው ዘርፎች መካከል አንዱና ዋነኛው እንዲሆን ተደርጓል። በዚህም የውጭውም ሆነ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች በራሳቸው አቅም ሆነ ተቀናጅተው የሚሠሩበትን የተመቻቸ ሁኔታ ለመፍጠር ተሞክሯል።

በሀገሪቱ የሚገኙ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን በየአካባቢው ከማስፋፋት ጀምሮ በኢንዱስትሪ ፓርኮቹ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች በስፋት የሚሳተፉበት የተመቻቸ ሁኔታ ተፈጥሯል። ግብርናን ከኢንዱስትሪው ጋር በማቀናጀት የዘርፉን ሀገራዊ አቅም ለማሳደግ ሰፋፊ ሥራዎች ተሠርተዋል።

ባለፉት አምስት ዓመታት በዓለም አቀፍ ደረጃ የተከሰተው የኮቪድ ወረርሽኝ ፣ የሰሜኑ ጦርነት እና በየአካባቢው የነበሩ የሰላም እጦቶች ዘርፉን ለማሳደግ በሀገር አቀፍ ደረጃ በተጀመሩ ጥረቶች ላይ ጉልህ ተጽእኖ አሳርፈዋል። በተጠበቀው መልኩ ውጤታማ እንዳይሆንም ተግዳሮት ሆነዋል።

ይህም ሆኖ ግን መንግሥት ለዘርፉ ከሰጠው ከፍ ያለ ትኩረት የተነሳ ፣ ዘርፉ ከፍ ባለ መነቃቃት ውስጥ የሚገኝበት ሀገራዊ ሁኔታ ተፈጥሯል። ለዚህም “ኢትዮጵያ ታምርት” በሚል በሀገር አቀፍ ደረጃ ተግባራዊ የተደረገው ንቅናቄ በዋኛነት ተጠቃሽ ነው።

ንቅናቄው በሀገሪቱ የሚገኙ ፋብሪካዎች ያሉባቸውን ችግሮች በጥናት በመለየት መፍትሄ ማፈላለግን መሠረት ያደረገ ፤ ፋብሪካዎቹ ባላቸው አቅም ወደ ምርት የሚገቡበትን መልካም አጋጣሚ በመፍጠር ምርታማነታቸውን በእጥፍ እስከ ማሳደግ የደረሰ ተሞክሮ መፍጠር ያስቻለ ነው።

በዚህም በዘርፉ የተሰማሩ ባለሀብቶችን የመሥራት መነቃቃት ከፍ ማድረግ ተችሏል። በዘርፉ የተሰማሩ ባለሙያዎች /ወዛደሮችም ጊዜያቸውን ፣ አቅም እና ክህሎታቸውን ተጠቅመው የተሻለ ተጠቃሚ የሆኑበት ተጨባጭ እውነታ ተፈጥሯል። ሀገሪቱም በቀጣይ ከዘርፉ ተጠቃሚ የምትሆንበትን ተስፋ በተጭባጭ አመላክቷል።

የዛሬውን የዓለም የወዝአደሮች ቀንን ስናከብር ፤ ዘርፉ የሀገሪቱ የኢኮኖሚ አቅም እንዲሆን በሁለንተናዊ መልክ የጀመርናቸው እንቅስቃሴዎች የበለጠ ስኬታማ እንዲሆኑ በተለይም ባለሀብቱ፣ ወዝአደሩ እና ሌሎች የዘርፉ ተዋንያን ከፍ ባለ የኃላፊነት መንፈስ ለመንቀሳቀስ ቃል እየገቡ ሊሆን ይገባል!

**አዲስ ዘመን**
ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ
ኢፕድ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የሆሣዕና ምስጋና

ኃይለማርያም ወንድሙ

ሆሣዕና በየዓመቱ የትንሳዔ በዓል ሊደርስ አንድ ሣምንት ሲቀረው ባለው እሁድ የሚከበር በዓል ነው። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ያሉ አብያ ክርስቲያናት የሆሣዕናን ዋዜማ ሌሊቱን በፀሎትና በማኅሌት (በምስጋና) ያሳልፉታል፡፡ ሲነጋ ደግሞ የኪዳን ፀሎትና ቅዳሴ ይደረጋል፡፡

ከቅዳሴ በኋላ ቀሳውስቱ እና ዲያቆናቱ የመጾር መስቀል (ትልቅ መስቀል) ይዘው በማዕጠንት እያጠኑ የሰንበት ትምህርት ቤት ህፃናት መዘምራን በከበሮ ታጅበው እየዘመሩ ቤተክርስቲያኑን ይዞራሉ፤ ይዘምራሉ፡፡ ምዕመናቱም ዘንባባ ይዘው እያወዛወዙ ሆሣዕናን ያከብራሉ፡፡

በዐቢይ ፆም ስምንት እሁድ ያሉ ሲሆን፤ ለእያንዳንዱ ሣምንት ስያሜ ያወጣው ቅዱስ ያሬድ ማህሌታይ መሆኑን የቤተክርስቲያን ሊቃውንት ይናገራሉ፡፡ በዚህም መሠረት ሳምንታቱ ዘወረደ፣ ቅድስት፣ ምኩራብ፣ መፃጉዕ፣ ደብረዘይት፣ ገብርኄር፣ ኒቆዲሞስ እና በሰሙነ ሕማማት ዋዜማ የሚከበረው ሆሣዕና በሚል ስያሜ ቅዱስ ያሬድ የሰየማቸው ሳምንታት ናቸው፡፡

የማቴዎስ ወንጌል አንድምታ ሆሣዕና ማለት መድኃኒት አሁን አድን ማለት ነው ይለዋል፡፡ ኢየሱስ የሚለውም ቃል ፍቺው መድኃኒት ማለት ነው፡፡ የደስታ ተክለወልድ ዐዲስ የማርኛ መዝገበ ቃላት ሆሣዕና የሚለውን ቃል ሲፈታው ከትንሳዔ በፊት ባለው እሁድ የሚከበር በዓል፤ ጌታችን ባህያ ተቀምጦ ሰሌንና የወይራ ቅጠል ይዘው ሆሣዕና እያሉ ስለተቀበሉት ቀኑ ሆሣዕና ተባለ፤ አሁን አድን ማለት ነው ይለዋል፡፡

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኀበር የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላትም ሆሣዕና፤ አሁን አድን ማለት ነው፡፡ የእስራኤል ሕዝብ የዘንባባ ዝንጣፊ ይዘው ‹‹ሆሣዕና›› መዝ. 118፥25፡26 በማለት እየጮሁ ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ አጀቡት፡፡ ማቴ. 21፥9-15፣ ማር.11፥9 ፣ዮሐ.12፥13 በማለት ያስረዳል፡፡

ቃሉን አይሁድና ክርስቲያኖች ለአምልኮ ቃልነት (liturgical) እንደሚጠቀሙበት ከድረ ገፅ የተገኙ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ሆሣዕና የአምልኮ ቃል መሆኑንና ስርወ ቃሉ ዕብራይስጥ ሲሆን በሮማይስጥና (ላቲን)፣ በግሪክ መጽሐፍ ቅዱስ ቃሉን እንዳለ እንደሚጠቀሙበት ያስረዳል፡፡ በግዕዝም፣ በእንግሊዝኛም በሌሎች ቋንቋዎችም ቃሉ ከዕብራይስጥ (አይሁድ) ወደ መጽሐፍ ቅዱስ እንዳለ የተወሰደ ነው፡፡

ሆሣዕና የዘንባባ በዓልም ተብሎ ይጠራል። ዘንባባ የድልና የሰላም ምልክት ነው፡፡ ይህም ጌታችን ኢየሱስ ለሰላም መምጣቱን ሲያመላክት ነው፡፡ አንድም ዘንባባ ጫፉ እሾኻም ነው፡፡ ኃያል ነህ አሸናፊ ነህ ሲሉት ነው። እስራኤል ደስ ሲላቸው ዘንባባ ይዞ የመዘመር ባህል ነበራቸው፡፡

እስራኤል ከግብፅ ባርነት በወጡ ጊዜ፤ ዮዲት የእስራኤልን ጠላት ሆሎፎርኒስን በገደለች ጊዜ ዘንባባ ይዘው ማመስገናቸውን ወንጌል አንድምታ ያስረዳል። ሆሣዕናም በእየሩሳሌም ዘንባባ ይዘው አዕሩግና ሕፃናት ያመሰገኑት የቀድሞውን ትውፊት ተከትለው ነው፡፡

ነገሥታት የሚሄዱት በፈረስ በበቅሎ ነው። አንድም ፈረስና በቅሎ ለጦርነት የሚጠቀሙበት ከቻሉ ጠላቶቻቸውን የሚያጠቁበት፣ የሚጠቁም ከሆነው በፈረስና በበቅሎ በፍጥነት ሊያመልጡበት ስለሚያስችል ነው፡፡ እየሱስ በተናቀችው አህያ ውርንጫላ ላይ ተቀምጦ ወደ እየሩሳሌም የገባው ለሰላምና ለትህትና መሆኑን ለማስገንዘብ እንደሆነ ሊቃውንቱ ያስረዳሉ፡፡

ህፃናት ጌታችን እየሱስ በአህያ እና በአህያይቱ ውርንጭላ ተቀምጦ ወደ እየሩሳሌም ሲገባ የሠላም ጌታ መጣ ብለው የወይራ ቅንጣፊ፣ የዘንባባ ዝንጣፊ ይዘው እያጀቡት አመስግነውታል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተጠቀሰው እየሱስ ሁለት ደቀመዛሙርቱን አህያ ከውርንጫዋ ጋር ከቤተ ፋጌ የድሆች መንደር ታስራ ታገኛላችሁ ፈታችሁ አምጡልኝ አለ፡፡

ማንም አንዳች ቢላችሁ፤ ለጌታ ያስፈልጉታል በሉ፤ ወዲያውም ይሰዳቸዋል፡፡ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 21 እንደተጠቀሰው ፤ ለጽዮን ልጅ ፡- እነሆ ንጉስሽ በአህያ ላይና በአህያይቱ ውርንጫላ ላይ ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመጣል ተብሎ በነቢይ የተነገረው ይፈፀም ዘንድ ነበር ሲል ይገልጻል፡፡ ይህም ነቢዩ ዘካሪያስ የተነበየው ሲሆን በትንቢተ ዘካርያስ 9፥9 ተጠቅሶ ይገኛል፡፡

በአብያተ ክርስቲያናት በሣሳዕና ህፃናትም ዘንባባ ይዘው አህያ ላይ ስዕለ እየሱስ አድርገው ከበሮ እየመቱ ቤተክርስቲያኑን እየዞሮ ይዘምራሉ። ከመዝሙራቱ መካከል

**“ሆሣዕና ሆሣዕና በአርያም**
**ብሩክ ሆሣዕና አምላከ እስራኤል**
**ተቀምጦ መጣ በአህያ ግልገል፡፡**
**በጣም ደስ ይበልሽ እልል በይ ጽዮን**
**ንጉሥሽ መጣልሽ ሊሆንሽ መድኅን …”**

መጽሐፍ ቅዱስ ላይ እንደተጠቀሰው፤ ለጌታችን ኢየሱስ አህያይቱንና ውርንጫዋንም አመጡለት፡፡ ልብሳቸውን በእነርሱ ላይ ጫኑ፤ተቀመጠባቸውም። ሕዝቡም በመንገድ ላይ ልብሳቸውን ጭምር አነጠፉ፡፡ በተጨማሪም ከዘንባባ ከቴምር እና ከወይራ ዛፍ ጫፍ ጫፍ እየቆረጡም አነጠፉለት ይላል፡፡ ወደ እየሩሳሌም ሲገባ ሆሣዕና ለዳዊት ልጅ በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው እያሉ ይጮኹ ነበር፡፡

በቤተክርስቲያን በሆሣዕና ዕለት ሲዘመርም የዐቢይ የፆም ወቅት የእየሱስ 40 ቀን የፆመበት ታስቦ ስለሚፆምና የመጨረሻው ሳምንት የመከራው ሳምንት የኀዘን ሣምንትም ስለሆነ ጭምር፤ የከበሮ መዝሙር አይዘመርም፡፡ ለሆሣዕና ግን በከበሮ ታጅበው ህፃናት ይዘምራሉ፡፡ ከመዝሙራቸው መካከል

**“…ሆሣዕና በአርያም**
**እያሉ ዘመሩ ህፃናት በኢየሩሳሌም**
**ሰላምሽ ዛሬ ነው ኢየሩሳሌም**
**ወዳንቺ መጥቷልና አምላክ ዘሳለም**
**አንቺ ቤተልሄም የዳዊት ከተማ**
**የሕዝቦችሽ ብርሃን መጣልሽ በግርማ**
**ሆሣዕና እያሉ አመሰገኑት**
**በኢየሩሳሌም አዕሩግ (አረጋውያን) ህፃናት**
**ኪሩቤል መንበሩን የሚሸከሙለት**
**መስቀል ተሸከመ ሊሆነን መድኃኒት…”**
**በግእዝም ሲዘምሩ**
**“ዲበ እዋል ተፂኢኖ**
**መፃ አምላከ አድኅኖ**

ሆሣዕና በደብረ ገሊላ›› ትርጉሙም በአህያ ውርንጫ ተቀምጦ፣ መጣ አምላክ ለአድህኖ ማለት ነው፡፡

በተለይ ህፃናቱ የዘንባባ ዝንጣፊና የቴምር ዛፍ ቅርንጫፍ ይዘው ይዘምሩ እንደነበር በአራቱም ወንጌላውያን ተጽፏል፡፡ እናም ህፃናት ሆሣዕና በአርያም (በሠማይ ያለ መድኃኒት) እያሉ የዘመሩበት ነበር፡፡ በዓሉ በአብያክርስቲያናቱ ሁሉ ቀሳውስትና ምዕመናቱ ሌሊት በማኅሌትና በፀሎት ቤተክርስቲያን ያሳልፉታል፡፡ በየዓመቱ ትንሳዔ አንድ ሳምንት ሲቀረው ባለው እሁድ ሆሣዕና ሲከበር ህፃናት ተሰብስበው የጌታ እየሱስን ስዕል በአህያ ላይ ይዘው ለሆሣዕና በዓል የተዘጋጁ ዝማሬዎች እየዘመሩ ቤተክርስቲያኑን ይዞራሉ፡፡

ከሰሌን ወይም ዘንባባ ዝንጣፊው የጣት ቀለበት ግንባር መስቀል በልዩ ቅርጽ እየሠሩ ያደርጋሉ፡፡ ካህናቱ ዲያቆናቱና ዘማሪ ህጻናቱ እንዲሁም ምዕመናን ሆሣዕናን እየዘመሩ ሲዞሩ ከአራቱ ወንጌሎች በአራቱም አቅጣጫ ሆሣዕናን አስመልክቶ የተጻፉ የወንጌል መልዕክቶች ይነበባል። ከዳዊት መዝሙር (ምስባክ) ማለትም እም አፈ ደቂቅ ወህፃናት አስተዳሎከ ስብሃት በእንተ ጸላዒ ከመ ትንስቶ ለጸላዒ ወለገፋኢ በግእዝ በዜማ ይባላል። ትርጓሜው ከህፃናትና ከሚጠቡ ልጆች አንደበት ምስጋናን አዘጋጀህ ስለጠላት ጠላትና ቂመኛም ለማጥፋት ማለት ነው፡፡

ሆሣዕና ሲከበርም እንደ መስቀል ደመራ እንደ ጥምቀት ከተራ ያለ ስዕላዊ በዓል በመሆኑ ውበቱ ልዩ ነው፡፡ ራሱን የቻለ የቱሪስት መስህብ ሊሆን የሚችል ታላቅ በዓል ነው፡፡ በዓሉ በከተሞች አካባቢ የደመቀ ቢመስልም በሁሉም ቤተክርስቲያን በውጪ ባሉትም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያና ሁሉ የሚከበር ነው፡፡

# ተጠየቅ

# «የአዲስ አበባን ተሞክሮ በመውሰድ በክልሉ ከተሞች የመልሶ ማልማት ሥራዎችን እየሠራን ነው»

- ኢንጂነር የማታለም ቸኮል፣
የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል
ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ ኃላፊ

ሙሉቀን ታደገ፣ ሞገስ ተስፋና መክሊት ወንደወሰን

**የደቡብ ምዕራብ ሕዝቦች ክልል እንደ ክልል ራሱን ችሉ ሲቋቋም በቢሮ ደረጃ ከተመሠረቱ መሥሪያ ቤቶች መካከል የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ አንዱ ነው፡፡ እናም በክልል የሚገኙ ከተሞች እንዲዘምኑና የከተማነት ደረጃ እንዲያሟሉ የማድረግ ኃላፊነት ለዚህ ቢሮ ተሰጥቷል፡፡**

**ከዚህ አንጻር የዛሬው የተጠየቅ ዝግጅታችን ቢሮው ባለፉት ሁለት ዓመታት ከተሞች በፕላን እንዲመሩ ለማድረግ ምን ሠራ? ምን ፈተናዎችስ ገጠሙት? አሠራሩን በማዘመን የሕዝብ ጥያቄዎችን ከመመለስ አኳያ ምን ጥረቶችን አደረገ በሚሉና ሌሎች ጉዳዮች ዙሪያ የአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍል የመልካም አስተዳደር እና ምርመራ ቡድን ከክልሉ ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ ኃላፊ ኢንጂነር የማታለም ቸኮል ጋር ቆይታ አድርጓል፡፡ መልካም ንባብ፡፡**

**አዲስ ዘመን፡- ባለፉት ሁለት ዓመታት ቢሮው ምን አቅዶ ምን ሠራ?**

**ኢንጂነር የማታለም፡-** ቀደም ብሎ በነበረው ሥርዓት የደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል ዋና መቀመጫ ሀዋሳ መሆኑ ይታወቃል፡፡ የሀዋሳ ከተማ የክልሉ ርዕሰ መስተዳደር መቀመጫ ከመሆኗ ባሻገር በክልል የሚገኙ የተለያዩ ቢሮዎች ይገኙባት ነበር፡፡ ይህም ከሀዋሳ ከተማ በርቀት ላይ የሚገኙ ዞኖችን እንዲሁም ከተሞችን ፍትሃዊ ተጠቃሚ እና በእኩል ደረጃ የልማት ተደራሽ እንዳይሆኑ አድርጓል፡፡

አሁን እንደ ክልል በተዋቀረው የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል የሚገኙ ከተሞች እና ዞኖች ፍትሃዊ የልማት ተጠቃሚ ሊሆኑ፤ እና በእኩል ደረጃ አስተዳደራዊ ተደራሽ ማግኘት አልቻሉም ነበር፡፡ ይሄን መነሻ በማድረግም በአሁኑ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል የሚገኙ ዜጎች የፍትዊ ተጠቃሚነት እና ተደራሽነት ጋር በተያያዘ ጥያቄ በማንሳታቸው፤ ጥያቄያቸው ተቀባይነት አግኝቶ ከሁለት ዓመት ተኩል በፊት ክልል መሆን ቻሉ፡፡

ከተሞችን ለማደግ በሚደረጉ የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የተደራሽነት ችግር የነበረባቸው። በሀዋሳ ዙሪያ ከሚገኙ ከተሞች አንጻር ብዙም ማደግ ያልቻሉ ናቸው፡፡ ይህ ሁነት የፈጠረውን ቁጭት መነሻ በማድረግ አሁን ላይ የክልሉ መንግሥት ያለውን ሀብት በመጠቀም እና ሕዝቡን በማሳተፍ በክልሉ የሚገኙ ከተሞችን ለማሳደግ በርካታ ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛል፡፡ ከእነዚህ መካከል የመሬት አቅርቦት እና ዝግጅት ሥራዎች በግንባር ቀደምትነት ተጠቃሽ ናቸው።

ከኢንቨስትመንት ጋር ተያይዞ ከዚህ በፊት ከነበረው የመሬት አቅርቦት እና አሠራር የተሻለ ነገር አለ፡፡ በአጠቃላይ ከመሬት ጋር ተያይዞ በአቅርቦትም በዝግጅትም ክልሉ እንደ ክልል የተሻሉ ሥራዎችን እየሠራ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- አዲስ ክልል እንደ መሆናችሁ የቅድሚያ ቅድሚያ የሰጣችሁት ተግባር ምንድን ነው?**

**ኢንጂነር የማታለም፡-** ሁሉም ሰው እንደሚገነዘበው ከመሬት ጋር ተያይዞ አሠራሩ በጣም ብዙ ፈተናዎች ያጋጥሙታል፡፡ ከመሬት ጋር የተገናኙ አሠራሮች ደግሞ በተፈጥሯቸው ሌብነት እና አድሎዓዊነት ይበዙበታል። ይህንን ዓይነት ፈተና የተሞላበትን ተቋም ደግሞ በሥርዓት እና በእቅድ መምራት ያስፈልጋል፡፡ ምክንያቱም መሬት ውድ ሀብታችን ነው፡፡ የከተሞቻችንም ትልቁ ሀብት መሬት ነው፡፡

እንደ ክልል መሬትን በአግባቡ ለመምራት እና ለመቆጣጠር በመጀመሪያ ደረጃ ትኩረት ተሰጥቶት የተሠራው የመሬት ምዝገባ ሥራ ነው፡፡ ከዚህ በፊት የከተሞቻችን የመሬት ምዝገባ ስንጀምር 500 «የመሬት ፓርሴሎች» ብቻ ነበሩ የተመዘገቡት፡፡ አሁን ላይ ግን ከስድስት ሺህ በላይ መመዝገብ ተችሏል፡፡ ከዚህ የበለጠ መሥራት ይቻል ነበር፡፡ ነገር ግን ክልሉ አዲስ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ባጋጠመው የሰው ኃይል እጥረት እና የሀብት ውስንነት ምክንያት በተፈለገው ልክ መሥራት አልተቻለም፡፡

በተለይ ከመሬት ምዝገባ ጋር ተያይዞ ያን ያህል ብዙ ሰርተናል ማለት አንችልም፡፡ ክልሉ እንደ ክልል ከመቋቋሙ በፊት ከነበረው ልምድ ሕብረተሰቡ መሬቱን የማስመዝገብ ፍላጎት አልነበረውም፡፡ ይሁን እንጂ ከምስረታ በኋላ ቢሮው ባከናወናቸው የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች አሁን ላይ የተሻለ ነገር አለ። በዚህም ቀድሞ ከነበረበት አኳያ ሥራውን ማሳደግ ተችሏል፡፡ ይሄ በመሆኑም ለነዋሪዎቹም ጭምር ዘርፈ ብዙ ፋይዳዎች አሉት፡፡

የከተማም ይሁን የገጠር መሬት ከተመዘገበ በቀላሉ ለብልሹ አሠራር እና ሌብነት አይጋለጥም፡፡ መንግሥትም ከወሰን ማስከበር እና መሰል ጭቅጭቆች ነፃ ይሆናል፡፡ የማዘጋጃም ሥራ ይቀንስለታል፡፡ በሕግ በተፈቀደለት አካል መሬቱን ያስመዘገበ ሰው ሀገሪቱ ብሎም ክልሉ የሚሰጧቸውን የተለያዩ አገልግሎቶችን እንዲያገኝ ያስችሉታል፡፡ የባንክ ብድር እና መሰል አገልግሎቶችን በቀላሉ ማግኘት ይችላል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- አሁን ላይ የሥራችሁ አፈጻጸም እንዴት ይገለጻል?**

**ኢንጂነር የማታለም፡-** አሁን ባለው ሁኔታ ጥሩ እየሄድን ነው፡፡ ከተሞች ከነበሩበት ድባቴ ወጥተው የተሻለ እንቅስቃሴ እያደረጉ ነው፡፡ ህብረተሰቡም የከተሞች እድገት የተሻለ እንዲሆን ከፍተኛ ጉጉት እና ፍላጎት አለው፡፡ ይሁንና ክልሉ አዲስ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ያጋጠመው የሰው ኃይል እጥረት እና የሀብት ጉድለቶች ቢሮው ሥራውን በተፈለገው ልክ ለማስኬድ አልቻለም፡፡ በቀጣይ ግን እነዚህን እጥረቶች ችግር ሆነው እንይዳነሱ ለማድረግ ከሚመለከተው አካል ጋር በጋራ ትኩረት ሰጥተን እየሠራን ነው፡፡ በተለይ የሠራተኞችን አቅም የመገንባት ሥራዎች በሰፊው እየተሠሩ ነው፡፡

ከመሬት ምዝገባው ጎን ለጎን የፕላን ማስከበር ሥራ በከፍተኛ ደረጃ እየተከናወነ ይገኛል፡፡ እንደ ክልል ከመመስረታችን በፊት የከተሞቻችን የፕላን ማስከበር ሥራዎች በአግባቡ የተሠሩ አልነበሩም፡፡ በመሆኑም በተለያዩ አካላት በርካታ ሕገ ወጥ ሥራዎች ይሠሩ ነበር፡፡ ለምሳሌ በፕላን በአረንጓዴ ሥፍራ እና መናፈሻነት የተመላከቱ ቦታዎችን መውረር፣ ትርፍ የመንግሥት ቦታዎች ማጠር እና በከተማ ዙሪያ በሚገኙ የአርሶ አደር ቦታዎች ላይ ከፕላን ውጭ የመስፈር ሁኔታዎች ነበሩ፡፡

ይህ አካሄድ ፕላንን የሚጣረስ በመሆኑ አሁን ላይ እንደ ክልል ፕላን የማስተግበር ሥራ እያከናወን ነው። ፕላን በደንብ ካልተተገበረ ሌብነት ይበራከታል፤ ሕገ ወጥ ሥራዎች ይስፋፋሉ፡፡ ይህ ደግሞ ውሃ፣ መብራት እና ሌሎች መሠረተ ልማቶችን ለህብረተሰባችን ማቅረብ እንዳይቻል እክል ይፈጥራል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- እስካሁን ምን ያህል መሬቶችን መመዝገብ ችላችኋል?**

**ኢንጂነር የማታለም፡-** አሁን በክልላችን በመንግሥት በኩል ሕጋዊ እውቅና እና ሰነድ የሌላቸውን ወደ 32 ሺህ የሚደርሱ የከተማ መሬቶችን መመዝገብ ተችሏል፡፡ ሆኖም ሙሉ በሙሉ ተጠቃሎ አልቋል ልማት አይደለም፡፡ አሁንም ያልተመዘገቡ የከተማ መሬቶች አሉ፡፡ እነሱን በመመዝገብ ሕጋዊ ለማድረግ እየሠራን ነው፡፡ ቢሮው ባከናወናቸው



ፎቶ-ሑዳሽ አብርሃ

ሥራዎች ሕጋዊ ሰርተፍኬት የሌላቸውን ቦታዎች እና ሰዎች ተለይተዋል። አሁን የሚቀረው የፕላን ጥሰት ያለባቸውን ሰዎች ከቦታው ማንሳት እንዲሁም የተነሱትን ደግሞ ቦታ በማዘጋጀት ማስፈር ነው። የፕላን ጥሰት የሌለባቸውን ደግሞ በሊዝ አሠራር መሠረት ወደ ተገቢው ሥርዓት የማስገባት ሥራዎችን እያከናወን ነው፡፡

በነገራችን ላይ ከመሬት ጋር ተያይዞ ችግሮች ሲነሱ እጁ የሌለበት ሰው የለም፡፡ ደላላው፣ አመራሩ፣ የተለያዩ ግለሰቦች እና ቡድኖች ይነካካሉ፡፡ ይህ ደግሞ የተጀመሩ ሥራዎችን በተፈለገው ልክ እንዳንጨረስ ሌላኛው ተግዳሮት ነው፡፡

የክልሉ ከተሞች ከተመሠረቱ በርካታ እድሜ ያላቸው ቢሆንም፣ ለበርካታ ጊዜያት ተረስተው እና ትኩረት ተነፍጓቸው መልማት ሳይችሉ ቆይተዋል፡፡ በአንጻሩ በሌሎች ክልሎች የሚገኙ ከተመሠረቱ አጭር እድሜ ያላቸው ከተሞች በከፍተኛ ፍጥነት ሲያድጉ እና ሲለወጡ ነበር፡፡ ይህን ሲሆን የበይ ተመልካች የነበረው ሕዝባችን «የእኛ ከተሞችስ በእነዚያ ከተሞች ልክ የማይለወጡት ለምንድን ነው?» በማለት ሲጠይቅ ነበር፡፡ ጥያቄው ደግሞ መልስ አግኝቷል። ጥያቄው መልስ ያገኘው ሕዝብም አሁን ላይ ከተሞች ተለውጠው እና አድገው ማየት ይፈልጋል፤ የሚፈልገው ለውጥ በአጭር ጊዜ እንዲመጣ በማሰብ ለክልሉ መንግሥት ድጋፍ እያደረገ ነው፡፡ በዚህም የቢሮውን ሸክም በተወሰነ ደረጃ እንዲቀል አድርጓል፡፡

በክልል ከተሞች የሚገኙ ነዋሪዎች ለከተሞቻቸው እድገት የሚደርገው አስተዋጽኦ በጣም ነው የሚበረታታው፡፡ የትኛውም አካባቢ ላይ ያለው ማህበረሰብ በጣም ለውጥን ይደግፋል፡፡ አሁን ኮብልስቶን በምንሰራባቸው አካባቢዎች፤ ዲሽ ቦዮች በአብዛኛው የምንሠራው ሕብረተሰቡ ባዋጣው ገንዘብ ነው፡፡ ምክንያቱም የሀብት ውስንነት አለ፡፡ አሁን ለምሳሌ ቦንጋ ላይ ድልድይ ለመሥራት ካሳ እየተከፈለ ነው፡፡ የካሳውን ክፍያ የከፈለው ሕዝቡ በራሱ አዋጥቶ ነው፡፡ መንግሥት ትንሽ ነው ያዋጣው፡፡ ኮንታ፤ ሚዛን፤ ቦንጋ፤ ጨና እና ሌሎችም የሕብረተሰቡ መነቃቃት ለአመራሩ ሞራል እየሆነን ነው፡፡ እንዳለ አመራሩ ይህንን ሞራል መጠቀም አለበት፡፡

መንግሥት ከየትም ሀብት አያመጣም፡፡ የመንግሥት የሀብት ምንጭ ከተለያዩ የግብር ዓይነቶች የሚሰበሰብ ሲሆን፤ የመሬት ግብር አንደኛው ነው፡፡ ስለሆነም ሕዝቡ መሬቱን አስመዝግቦ ሕጋዊ በመሆን ለመንግሥት ግብር መክፈል አለበት፡፡ ሁሉም ሰው መሬትን በሕጋዊነት ሊጠቀም ያስፈልጋል፡፡ አብዛኛው መሬታችን በማዘጋጃ አልተመዘገበም፡፡ ስለሆነም ሕዝባችን መሬቱን አስመዝግቦ ሰርተፍኬት መያዝ እና በትክክል ለመንግሥት ግብር መክፈል አለበት። ምክንያቱም መንግሥት ከግብር የሰበሰበውን ገንዘብ የትም አይወስደውም፡፡ እዚያው ውሃ፤ መብራት፤ መንገድ ነው የሚሠራበት፡፡

እኛም፣ እንደ ሀገር በአዲስ አበባ የጀመረውን ከተሞችን መልሶ የማልማት ሥራ እንደተሞክሮ በመውሰድ በክልሉ በሚገኙ ከተሞች የመልሶ ማልማት ሥራዎችን እየሠራን ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በቦንጋ እና በሚዛን አማን ከተሞች አበረታች ጅምሮች አሉ፡፡ በመልሶ ማልማቱ ተነሽ ለሆኑ ሰዎች ቦታ ተዘጋጅቶላቸዋል፡፡

ሕብረተሰቡ ከተሞች እንዲለሙ እና እንዲለወጡ ባለው ጉጉት የተነሳ የተጋነነ ካሳ አይጠይቅም፡፡ ይሁን እንጂ እንደ መንግሥት ካሳ እያዘጋጀን ነው፡፡ ሥራው የተሳለጠ እንዲሆን እና የካሳ ክፍያው ሳይቆራረጥ እንዲሠራ ለማድረግ ሕብረተሰቡ በፍላጎቱ ገንዘብ እያዋጣ ነው፡፡ እንደ ሀገር የተጀመረው ከተሞችን የመልሶ ማልማት ሥራዎች የሕዝባችንን አስተሳሰብ የለወጡ መሆናቸውን ያየንበት ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ከተማዋን የቱሪስት መዳረሻ**

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# ተጠየቅ

## «የአዲስ አበባን ተሞክሮ በመውሰድ...

ከገጽ 6 የዞረ

**ስማድረግ ምን እየተሠራ ነው?**

**ኢንጂነር የማታስም፡-** ከተማዋን የሚመጥኑ እና ቱሪስቶችን ሊስቡ የሚችሉ ሥራዎች እየተሠሩ ነው፡፡ ፕላንን መሠረት ያደረጉ ለቱሪዝም ጉልህ አስተዋጽኦ ያላቸው ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ ከቱሪዝም ጋር ተያይዞ የአስተሳሰብ ለውጥ ሕብረተሰቡ ላይ ተፈጥሯል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ክልሉ አዲስ እንደመሆኑ ቢሮው ምን ፈታናዎች ገጠሙት ?**

**ኢንጂነር የማታስም፡-** ሁሉምእንደሚያውቀው ክልሉ ውስን ሀብት ነው ያለው፡፡ ከፌዴራል የሚበጀተውም ሆነ ከቢሮው የሚሰበሰበውም ሀብት በጣም ውስን ነው፡፡ ደቡብ ክልል በነበርንበት ጊዜ የተጀማመሩ ነገር ግን ያልተጠናቀቁ፤ በርካታ ገንዘብ የሚፈልጉ ሰፋፊ መሠረተ ልማቶች አሉ፡፡ በተለይም በኮንስትራክሽን ዘርፍ፣ የጤና ጣቢያ ግንባታ የቴክኒክ እና ሙያ ግንባታዎች እንዲሁም መንገዶች አሉ፡፡

እነዚህ ሳይጠናቀቁ ነው ወደ ክልልነት የመጣነው። አሁን ባለው ሁኔታ እነዚህን ፕሮጀክቶች ማጠናቀቅ የክልሉ ፈተና ሆኗል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ የሀብት ውስንነት መኖሩ ነው፡፡ አሁን ላይ ለክልል የሚመደበው በጀት ከደመወዝ ተርፎ ለልማት የሚውል አይደለም። በመሆኑም አሁን ላይ ክልሉ እንደ ክልል እና ከተማ ልማት እና ኮንስትራክሽን ቢሮ በበጀት እጥረት እየተፈተኑ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የቦንጋ ከተማን በከተሞች መስፈርት ልክ ለመገንባት ምን እየተሠራ ነው?**

**ኢንጂነር የማታስም፡-** ቦንጋ ለመልማት ብዙ ኢንቨስት ማድረግን የማትጠይቅ ከተማ ናት፡፡ ያላት የተፈጥሮ ሀብት ላይ የተወሰነ ኢንቨስት ቢደረግ ማራኪ እና ምቹ ከተማ ማደረግ ይቻላል፡፡

ከተማዋን ለመቀየር ትልቁ ነገር አስተሳሰብ ነው። በቀላሉ መለወጥ እንደሚቻል ማመን ያስፈልጋል። ይህንን ለሕዝቡ ማስገንዘብ ይጠይቃል፡፡ ለልማት የሚሳሳ አመራር መፍጠር የግድ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ለኢንቨስትመንት የተሰጡ የከተማ ቦታዎች ምንም ልማት ሳይከናወንባቸው እንዲሁ ታጥረው ይቀመጣሉ፡፡ በእነዚህ ኢንቨሰተሮች ላይ በተጨባጭ ምን ዓይነት ርምጃዎችን እየወሰዳችሁ ነው?**

**ኢንጂነር የማታስም፡-** ከዚህ ቀደም በኢንቨስትመንት ስም ለባለሀብቶች የተሰጡ መሬቶች በአግባቡ እንዲለሙ ከባለሀብቶቹ ጋር እየተነጋገርን ነው፡፡ በተቻለ መጠን ወደ ግንባታ እንዲገነቡ የማድረግ ሥራዎችን እያከናወን ነው፡፡ ይህንን ማድረግ የማይችሉትን ሥርዓት የማስያዝ ርምጃዎችን እየወሰድን ነው፡፡ ከዚህ ቀደም በነበረው ነባራዊ ሁኔታ ለባለሀብቶች አንድ ጊዜ መሬት ከተሰጠ በኋላ ክትትል አይደረግም፡፡ ይህ ደግሞ ባለሀብቱ መሬቶችን አጥሮ ሳያለማ እንዲቀመጥ አድርጎታል፡፡ አሁን ላይ ይህንን የማስተካከል ሥራ እየሠራን ነው፡፡

አሁንም በኢንቨስትመንት ላይ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተን እየሠራን ነው፡፡ ‹‹አቅም አለኝ ማልማት እችላለሁ›› የሚል አካል ሲመጣ በራችን ክፍት ነው። ከክልል እስከ ዞን ኢንቨስተሮች በከተሞች ልማት ዙሪያ ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ ፍላጎቱ አለን፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የተጀመሩ ነገሮች አሉ፡፡ ሆቴሎች በየቦታው እየተጀመሩ ነው፤ ግንባታቸው ተጠናቆ የተመረቁም አሉ፡፡

በአጠቃላይ መገንባት ያቃታቸው ላይ ርምጃ እየወሰድን ነው፡፡ አዲስ የሚመጡ ባለሀብቶችን ለማበረታታት አገልግሎታችንን የማሻሻል ሥራዎች እንሠራለን፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የቦንጋ ከተማ የክልሉ መቀመጫ እንደመሆኗ ባለሀብቶች የሪል ስቴት ቤቶችን እንዲገነቡ ለማድረግ ምን የታሰበ ነገር አለ?**

**ኢንጂነር የማታስም፡-** ሪል ስቴቶችን የሚሠሩ ባለሀብቶችን ክልሉ ይፈልጋል፡፡ በሪል ስቴት ብቻ ሳይሆን በሌሎች መስኮችም የክልሉ ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽንየቢሮ ባለሀብቶችን ለመሳብ ጥረት እያደረገ ነው፡፡ ነገር ግን እስካሁን በቦንጋ ከተማ ላይ



ምንም የተጀመረ ነገር የለም፡፡

ከዚህ ጉዳይ ጋር በተገናኘ እንደ ቢሮ ሰርተናል ብዬ አልገምትም፡፡ ስለዚህ ቀሪ ሥራችን እንዴት ባለሀብቶችን እንሳብ የሚለው ይሆናል፡፡ የሕግ ማቀፎችም ስለሚያስፈልጉ የሕግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት ይኖርብናል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በክልሉ መዲና እና በዞን ከተሞች የጋራ መኖሪያ ቤቶችን (ኮንዶሚኒየሞችን) ስመሥራት ምን አቀዳችሁ?**

**ኢንጂነር የማታስም፡-** በክልሉ የሚገኙ የተለየዩ የመንግሥታዊ ተቋማትን ሰው ኃይል እንኳን ለመሙላት የሀብት እጥረት አለብን፡፡ ክልሉ አዲስ እንደመሆኑ ለሕዝቡ ማሟላት የነበረባቸውን ነገሮች እንኳን ያላሟላናቸው በርካታ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፣ ቦንጋ ከተማ ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የውሃ ችግር አለ። በክልሉ አስቸኳይ የጤና ጣቢያ እና ሆስፒታል የሚያስፈልጋቸው ቦታዎች በርካታ ናቸው፡፡ መንገድ እና መሰል የመሠረተ ልማቶችም የክልሉ ፈተናዎች ናቸው፡፡ ስለሆነም የጋራ መኖሪያ ቤት ለመገንባት ከማሳበችን በፊት እነዚህን የሕዝብ ጥያቄዎች መመለስ ያስፈልጋል፡፡ ይሁን እንጂ በክልሉ በስትራቴጂክ ፕላን ደረጃ የጋራ መኖሪያ ቤት ለመገንባት ፍላጎቱ አለን። ነገር ግን አሁን ላይ ለማድረግ አስቸጋሪ ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ ዘርፍ መሰማራት የፈለገ ባለሀብት ካለ ለማስተናገድ በራችን ክፍት ነው፡፡

በነገራችን ላይ የከተማ ልማት ሚኒስቴር እስከታች መዋቅር ድረስ አደረጃጀት አለው፡፡ ከዚህ አንጻር በሁሉም ደረጃ የሚገኙ መዋቅሮች መንግሥት ፖሊሲ ጋር የተናበቡ ናቸው፡፡ የአቅም ውስንነት ካልሆነ በቀር በፌዴራል ደረጃ የሚሠሩ ሥራዎች እስከታችኛው መዋቅር ድረስ በሚገኙ በከተሞች ይሠራሉ፡፡ የአቅም ውስንነት ግን የትኛውን ቅድሚያ ሰጥቼ ልሠራ የሚለውን ፈተና ያደርገዋል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በነባር ክልሎች ልክ አገልግሎቶቻችሁን ስሀገር ውስጥና ስውጭ ሰዎች በቀላሉ ተደራሽ ስማድረግ የአውሮፕላን ጣቢያዎች በክልላችሁ እንዲኖሩ ስማድረግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ምን እየሰራችሁ ነው?**

**ኢንጂነር የማታስም፡-** አዎ! አገልግሎቶቻችን ተደራሽ ለማድረግ ከተለያዩ አካላት ጋር የአውሮፕላን ጣቢያ እንዲኖረን ለማድረግ በርካታ ሥራዎችን እየሠራን ነው፡፡ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ ሚዛን አማን ከተማ ላይ እየተሠራ ነው፡፡ በቦንጋ ከተማም የሄሊኮፕተር እና ቀላል አውሮፕላን ማረፊያ እየተሠራ ነው፡፡ ሌሎች ከተሞችም ላይም ፍላጎቱ አለ፡፡ ቴፒ ላይ የግል አውሮፕላን እያረፈ ነው፡፡ የሚዛን እና ቦንጋ የአውሮፕላን ማረፊያ ግንባታ ፕሮጀክቶች በጥሩ ደረጃ ላይ ይገኛሉ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- አዲስ ክልል ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ከየሴክተር መሥሪያ ቤቶች ጋር ተናቦ ከመሥራት አንጻር በተጨባጭ ምን እየሰራችሁ ነው ?**

**ኢንጂነር የማታስም፡-** ከሴክተር መሥሪያ ቤቶች ጋር ተናቦ መሥራት ግዴታ ነው፡፡ ተናቦ መሥራት ካልተቻለ ነገሮች ሁሉ ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ ነው የሚሆኑት፡፡

በከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር መንገድ፣ ቴሌ፣ ውሃ ልማት እና መብራት በራሱ አቀናጅቶ በኦንላይን ነው የሚመራው፡፡ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ግን መንገድና ትራንስፖርት የራሱ ቢሮ አለው፡፡ የውሃ ልማትም ለብቻው የራሱ ቢሮ አለው፡፡ ቴሌና መብራት ደግሞ በርዕሰ መስተዳደሩ ልዩ አማካሪ ስር ነው የሚተዳደሩት። ስለዚህ የተቀናጀ እና ተናብቧ ሥራ ለመሥራት መሥሪያ ቤቶችን ትንሽ ሰብሰብ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ይሁን እንጂ ከአዲስ ከመሆኑ አንጻር አስተማማኝ ነው ባልልም ግን ቅንጅቱ በጥሩ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡

በፌዴራል ደረጃ በየጊዜው መድረኮች አሉ፡፡ በመሆኑም ሴክተር መሥሪያ ቤቶች በቅንጅት ተናበው ይሠራሉ፡፡ አሠራራቸውም ተቋማዊ ነው፡፡ እኛ ላይ ግን ተቋማዊ ከማድረግ አኳያ ክፍተቶች አሉ፡፡ ይሁን እንጂ እያንዳንዱን መሠረተ ልማት በፕላኑ መሠረት ይመራል። ገጠር ላይ እስካሁን እንደዚህ ዓይነት ፈተና የለም፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ከልማት ተነሽዎች ጋር በተያያዘ ምን ችግር ገጠማችሁ? የልማት ተነሽዎች ልማቱ የኔ ነው ብለው እንዲስቡ ከማድረግ አኳያ ምን ያህል ግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን ሰርታችኋል ?**

**ኢንጂነር የማታስም፡-** እስካሁን የጎላ ችግር አልገጠመንም፡፡ ምክንያቱም ከልማት ተነሺ ማህበረሰባችን ጋር በተደጋጋሚ ውይይቶችን አድርገናል፡፡ አሁን ቦንጋን ከተማ አስተዳደርን እንኳን ብንወስድ ከመልስ ማልማቱ ጋር ተያይዞ ያልተወያየ ዜጋ የለም፡፡ ሁሉም የሕብረተሰብ ክፍል ተወያይቷል። ይህን በማድረጋችን ማህበረሰባችን ለልማቱ ያለውን አመለካከት በአውንታዊ መልኩ መቀየር ተችሏል፡፡ በዚህም ለልማት ተነሺዎች ከኪሱ ገንዘብ አውጥቶ ካሳ መክፈል የቻለ ማህበረሰብ ፈጥረናል፡፡ ስለዚህ ያን ያህል ፈታኝ ችግር አልተፈጠረም፡፡

አልፎ አልፎ ከራሳችን ብልሹ አሠራር አጋር ተያይዞ የተለያዩ አላስፈላጊ ነገሮች ሲፈጠሩ ይታያል። እነዚህን ችግሮች በጥንቃቄ እንዲታዩ እና በአጠረ ጊዜ እልባት እንዲያገኙ ለማስቻል ራሱን የቻለ ኮሚቴ ተዘጋጅቷል። ከዞን ጀምሮ እስከ ላይኛው ድረስ መዋቅሮች ተዘርግተዋል፡፡ የክልሉ ቢሮም እስከታች ድረስ ወርዶ ቅሬታ የሚፈታበት ሁኔታ አለ፡፡ ነገር ግን ከተሞች እንዲለሙ የሕዝቡ ፍላጎት ከፍተኛ በመሆኑ ያን ያህል የተጋነነ ችግር አልገጠመንም። እስካሁን በመጣንበት እና በተከተልነው አሠራር ሕዝቡ ደስተኛ ነው፡፡ ምን አልባት በግለሰብ ደረጃ ግን የሚነሱ ቅሬታዎች ይኖራሉ። በግለሰብ ደረጃ ብዙ ጊዜ የሚነሳው ቅሬታ ንብረቴን እስከማነሳ ጊዜ ይሰጥኝ የሚል ነው፡፡

ማዘጋጃ ቤቱ ከሌብነት ነፃ ነው ብሎ ማንም ሰው በትክክል ሊገመግም አይችልም፡፡ ብዙ ነገሮች ገና ይቀሩታል፡፡ ስለዚህ የማዘጋጃ ቤትን ሥርዓት ማስያዝ እና የሠራተኛውን አመለካከት በመቅረጽ ከሰው ንክኪ ነፃ የሆነ የዲጂታል አሠራር ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡ ከመሬት ምዝገባ አገልግሎት እና የሕንፃ አዋጅን ተግባራዊ ከማድረግ ጋር ተያይዞ ከእጅ ንክኪ ነፃ ለማድረግ የጀመርናቸው ነገሮች አሉ፡፡

በሌሎች አገልግሎቶች ላይ ወደ ሲስተም ለመግባት ግን አሁንም ዳተኝነት አለ፡፡ ከሕዝብ የሚመጣውን ቅሬታ ግን ለመፍታት ሰው እንደፈለገ ሊያደርገው ከሚችለው የቆየ አሠራር መውጣት ያስፈልጋል፡፡ ሁሉም ነገር ዲጂታላይዝድ ተደርጎ ቢሠራ ከሕዝባችን የሚነሱ ችግሮችን በቀላሉ መፍታት እንችላለን፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ሥራዎችን ወደ ዲጂታል ስማስገባት ከሌሎች ክልሎች እና ሀገራት ልምድ ከመለዋወጥ አንጻር ያላችሁ ተሞክሮ ምን ይመስላል?**

**ኢንጂነር የማታስም፡-** በክልሉ ቢሮ ስር የሚገኙ አሠራሮችን ለማዘን እንቅስቃሴ ላይ ነን፡፡ ለምሳሌ የቦንጋን የመሬት አስተዳደር ጉዳይ ሙሉ በሙሉ ዲጂታላይዝድ ለማድረግ እየተሠራ ነው፡፡ ከዚህ በኋላ የመሬት ጉዳይ ‹‹በኮምፒውተር ሲስተም›› ይሠራል። በሌሎች ከተሞች ላይ ውጤታማ የሆኑ በከተማና ልማት ሚኒስቴር የተረጋገጡ ተሞክሮዎን በሶፍትዌር ዴቨሎፕ አድርገን በቦንጋ እና ሚዛን ማዘጋጃ ቤቶች ላይ እየዘረጋን ነው፡፡ ኔትወርክ ዘርግተን ባለሙያዎች እና ቁሳቁሶችን አሟልተን ሙከራ ጀምረናል፡፡

የመረጃ አያያዝ ሥርዓታችን ደካማ በመሆኑ የተለያዩ ፋይሎች የት እንዳሉ እንኳን አይታወቅም፡፡ በመሆኑም በሁሉም ከተሞች ላይ ሰነዶችን ‹‹ስካን›› ተደርገው ወደ ‹‹ሶፍት ዶክመንት›› ተቀይረው እየተደራጁ ነው። ሶፍትዌር ዴቨሎፕ አድርገው ወደ ትግበራ መግባት የማይችሉ የሥራ ክፍሎች አቅም አግኝተው ወደሲስተም እስኪገቡ ድረስ ይህንን እያደረጉ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ቢሮው ከቦንጋ ዩኒቨርሲቲ ጋር ተባብሮ ከመሥራት አንጻር ያለው ሂደት እንዴት ይገለጻል?**

**ኢንጂነር የማታስም፡-** በከተማችን የቦንጋ ሙዚየም ይገኛል፡፡ ይህን ሙዚየም በማልማት ሕዝቡን ተጠቃሚ ከማድረግ አኳያ ከዩኒቨርሲቲው ጋር በትብብር እየሠራን ነው፡፡ ከቦንጋ ዩኒቨርሲቲ ማህበረሰብ ከተማው የነሱ እንደመሆኑ መጠን መዋቅሮቻችን የሚጠይቋቸውን ድጋፎች በአቅማቸው ያደርጋሉ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ስስነበረን ቆይታ እናመሰ ግናስን፡፡**

**ኢንጂነር የማታስም፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

# ሃሳብ፣ ኃይል፣ ትጋትና ቁርጠኝነት በአንድ ላይ የሚገኙት ወጣቱ ጋ ነው

ቴልጌልቴልፌልሶር (የኩሽ አሽከታብ)

ወጣቱን ከልማት እና ከሥራ ፈጣሪነት ጋር ያጣመረ አዲሱ የስታርት አፕ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት ልዩ ድጋፍ ተሰጥቶት በሀገር አቀፍ ደረጃ ተጀምሯል፡፡ ይሄ አዲስ ወጣት ተኮር እንቅስቃሴ ማህበረሰቡን ከሃሳብና ከሥራ ፈጣሪነት ጋር አዋህዶ የኢኮኖሚ ግስጋሴን የሚያፋጥን ነው። ከጥቅም አኳያም የብዙሃኑን ሕይወት የሚቀይር፣ ወጣት ባለሀብቶችን ከመፍጠር፣ ከፍተኛ ግብር ከፋዮችን ከማፍራት እና ሀገርን ከድህነት ከማውጣት አኳያ ላቅ ያለ ተስፋ ያለው ነው፡፡

አፍሪካን ጨምሮ ብዙ የዓለም ሀገራት በዚህ ወጣት ተኮር የሥራ ፈጣሪነት ጽንሰ ሃሳብ ስር ኢኮኖሚያቸውን በማሳደግ ማህበረሰባቸውን ከተረጂነት የታደጉ ጥቂቶች አይደሉም፡፡ በቀጣይም ብዙዎች እንደ አንድ የኢኮኖሚ ማነቃቂያ አድርገው ሊጠቀሙበት እንቅስቃሴ ላይ ይገኛሉ፡ የዚህ ንቃት ተሳታፊ ከሆኑ ሀገሮች ውስጥ ደግሞ ሀገራችን ኢትዮጵያ አንዷ ሆናለች ፡፡

ለዘመናት ያለንን የወጣት ኃይል ሳንጠቀምበት፣ ሥራ ፈጣሪዎችን ሳናበረታታ፣ በእውቀታችንና በተፈጥሮ ሀብታችን ሳንጠቀም፣ መሥራትና መቀየር እየቻልን ግን ሳንቀየር ሰንብተናል፡፡ ለዚህ እንደ ዋና ምክንያት ከሚጠቀሱት ውስጥ የወጣቱን አቅም በአግባቡ መጠቀም የሚያስችሉ እድሎችን/አስቻይ ሁኔታዎችን መፍጠር አለመቻላችን ነው፡፡

በቀደሙት ጊዜያት የነበረው ሀገራዊ እውነታ የፈጠራ ሃሳቦችን ይዞ በቀላሉ ወደ ሥራ መግባት የሚያስችል አልነበረም፡፡ አይደለም ለጀማሪ ሥራ ፈጣሪ ቀርቶ በዘርፉ ላይ ለሰነበቱ እንኳን ተግዳሮቱ የበዛ ነበር፡፡

በዚህ ምክንያት እንደ ሀገር፣ እንደ ማህበረሰብ፣ እንደ መንግሥት ብዙ ጥቅሞች ቀርተውብናል፡፡ ራሳችን ጠቅመን ሌሎችን የምንጠቅምበት ሃሳብ፣ ተሰጥኦ፣ የሥራ ፈጣሪነት ወኔ ሁሉ እንዳልነበረ ሆኗል፡፡

መንግሥት እነዚህን ሁሉ ነባር ችግሮች በመመልከት ከዛም በላይ ጊዜና ቦታ በመስጠት በሰፋና በዳበረ መጪውን ጊዜ ብሩህ ማድረግ በሚያስችል የስታርትአፕ ጽንሰ ሃሳብ ወጣቱ ራሱን ጠቅሞ ለሌሎች የሚተርፍበትን አቅጣጫ ቀይሶ ወደ ሥራ ገብቷል፡፡ ይህ የመንግሥት መነሳሳት በቀጣይ የወጣቱን የመፍጠር፣ የማሰብ፣ የመከወን ትኩስ ኃይል ለሀገር ግንባታ ለመዋል የሚያስችል እንደሆነ ይታመናል፡፡

ይሄን መሰሉ በመንግሥት በጀትና አቅጣጫ እየተመራ ያለ ወጣት ተኮር እንቅስቃሴ ለትውልዱ ተስፋ ከመሆን በተጨማሪ ሞዴልና አርአያ የሚሆኑ ወጣት ባለሀብቶችን በመፍጠር ረገድ የጎላ ሚና የሚኖረው ነው፡፡ ወጣቱን በገንዘብ፣ በእውቀት፣ በክህሎት፣ በቴክኖሎጂ፣ በሥራ ፈጣሪነት ከዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ጋር ለማስተሳሰር የተሻለ አማራጭ ሆኖ የሚያገለግል ነው፡፡

ሀገርና ወጣት፣ ማህበረሰብና ወጣት፣ ልማትና ወጣት፣ ፖለቲካና ወጣት በአንድ የተሳሰሩ አንዳቸው ያለአንዳቸው ብቻቸውን መጽናት የማይችሉ እውነቶች ናቸው፡፡ ለወጣቱ እድል መስጠት ማለት ብዙ የተዘጉ ሀገራዊ በሮችን መክፈት ማለት ነው፡፡

ወጣት ያልሳተፈበት ልማት፣ ያልተሳተፈበት ፖለቲካ፣ ያልተሳተፈበት ዲፕሎማሲያዊና ማህበራዊ መስተጋብር ሊኖር አይችልም፤ ይኖራል ተብሎ ቢታሰብ እንኳን የጸና ሊሆን አይችልም። እኛ ደግሞ በወጣት ሀይላቸው ከታደሉ ጥቂት የዓለም ሀገራት ግንባር ቀደሞቹ ነን፡፡

እንደ ስታርት አፕስ ያሉ ሀገራዊ እንቅስቃሴዎች ይህንን ኃይል በዋነኛነት በማሳተፍ፤ በሥራ ፈጣሪነት ተጀምረው በትላልቅ ዓለም አቀፍ ተጽዕኖ ፈጣሪነት የሚቀጥሉ ናቸው፡፡ መነሻቸው ሀገር ቢሆንም መድረሻቸው ዓለም አቀፋዊነት ነው፡፡ ከሃሳብ መንጭተው፣ በሃሳብ ዳብረው በኢኮኖሚና በተሰሚነት ለሀገር ሉዓላዊነት ዘብ የሚቆሙ ናቸው። ከራስ በሆነ ታታሪነት ለብዙዎች እንጀራ በመሆን በሀገር ላይ በጎ ዐሻራን ማስቀመጥ የሚያስችል ነው።

**በስታርት አፕ የሥራ ፈጠራ ዘርፍ ውጤታማ ለመሆን እንደ ቅድመ ሁኔታ የተቀመጡ አራት የ‹መ› ሕጎች መኖራቸው በባለሙያዎቹ ይነገራል። የትኛውም የሥራ ዘርፍ ውጤት ተኮር ሆኖ እንዲቀጥል ‹ፍላጎት፣ ትጋት እና ተስፋ አለመቁረጥ› አስፈላጊዎቹ እንደሆኑ ይታመናል፡፡ ከዚህ እውነታ ጋር በማቆራኘት የስታርት አፕን አራት የውጤታማነት ሕጎች ማንሳት ተገቢ ነው**

ኢትዮጵያን ያለ ወጣቱ እንቅስቃሴ ማሰብ ሻማን ያለ ክር ለማብራት ከመሞከር ጋር አንድ ነው፡፡ ሻማ ያለ ክር እንደማይበራ ሁሉ ሀገርም ያለ ወጣት ንቃት ምንም ናት፡፡ ወጣቱን ማንቃት ሀገርን ማንቃት፣ ማህበረሰቡን ማብቃት ነው፡፡ ትውልዱን ማንቃት ኢኮኖሚውን፣ ፖለቲካውን፣ ዲፕሎማሲውን፣ ማህበራዊ መስተጋብሩን ማንቃት ነው፡፡ ወጣቱን ማሳተፍ ሰላምን ማምጣት፣ አንድነትን ማወጅ፣ ወንድማማችነትን ማስቀደም ነው፡፡

ስታርት አፕ ደግሞ ለዚህ ፍቱን ሆኖ የቀረበ ከወጣቱ በወጣቱ የሆነ አስተሳሰብ ነው፡፡ አንቂና አበረታች ያልሆነውን የሥራ ፈጣሪነት ሥርዓቶች በመቅረፍ ወጣቱን በሃሳብ፣ በሥራ ፈጣሪነት፣ በእውቀትና በምክንያታዊነት ወደ ሀገራዊ ተሳትፎ የሚያስገባ የእድልና ድል መንታ ገጽ ነው። አሁን ባለው ወቅታዊ ሁኔታ ለወጣቱ እጅግ የተሻለ የለውጥና ራስን የመግለጫ መድረክ ሆኖ የሚያገለግል ነው፡፡ ሃሳብ ይዞ መንገድ ላጣው፣ በዚህም ተስፋ ሊቆርጥ ለተቃረበው ወጣት ድል ማድረጊያ ፍኖቱም ነው፡፡

ስታርት አፕ ሃሳብና ቴክኖሎጂ የተዋሃዱበት ዘመን ወለድ አስተሳሰብ ነው፡፡ ማንኛውም በአነስተኛ የሥራ መስክ የተጀመረ የሥራ ዓይነት ካለ ቴክኖሎጂ ብቻውን ስታርት አፕ ሊባል አይችልም።ከቴክኖሎጂ መስፋፋትና መናር ጋር አብሮ የመጣ አዲስ እና ወጣት ተኮር የሥራ ንቃት ነው፡፡

በስታርት አፕ የሥራ ፈጠራ ዘርፍ ውጤታማ ለመሆን እንደ ቅድመ ሁኔታ የተቀመጡ አራት የ‹መ› ሕጎች መኖራቸው በባለሙያዎቹ ይነገራል። የትኛውም የሥራ ዘርፍ ውጤት ተኮር ሆኖ እንዲቀጥል ‹ፍላጎት፣ ትጋት እና ተስፋ አለመቁረጥ› አስፈላጊዎቹ እንደሆኑ ይታመናል፡፡ ከዚህ እውነታ ጋር በማቆራኘት የስታርት አፕን አራት የውጤታማነት ሕጎች ማንሳት ተገቢ ነው፡፡

የመጀመሪያው ሊሰሩት ያሰቡትን የሥራ ሃሳብ መውደድ ነው፡፡ የምንወደው ነገር ትጋትና ንቃትን አለመዛልንም በማጎናጸፍ ወደፊት የሚወስደን እንደሆነ ይታመናል፡፡ የትኛውም ሥራ ፈጣሪ በሚወደው ሥራ ዘርፍ ላይ ሆኖ ደከመኝና ታከተኝ ሊል የሚችልበት አጋጣሚ አይኖርም፡፡ በዚህም የተነሳ ለመሥራት ያሰብነውን ሥራ መውደድ መቻል እንደ መጀመሪያ የስታርት አፕ የውጤታማነት የመ ሕግ ሆኖ ከፊት ይመጣል፡፡

ሁለተኛው መቻል ነው፡፡ አንድን ነገር ወደ ስኬታማነት ለመቀየር ከመውደድ እኩል መቻል ያስፈልጋል፡፡ የወደድነውን ነገር ካልቻልነው መውደዳችን ብቻውን ውጤት አያመጣም፡፡ የምንወደውን ነገር ወደመሆን የሚቀይር የብቃትና የፈጻሚነት መቻል ግድ ይላል፡፡ ዛፍ እንወዳለን ብንል የምንወደውን ዛፍ እውን ሆኖ ለማየት አሊያም በጥላው ለመጠለል ዛፉን መትከል መቻል አለብን፡፡ ዛፍ መውደድ ቀዳሚው ሲሆን ዘር ዘርቶ ዛፍ ማብቀል ግን የድርጊት ውጤት ነው፡፡ መውደድ እና መቻል በአንድ ላይ ሲመጡ በዚህ ምሳሌ መቃኘት ይችላሉ፡፡

ቀጣዩ መፈለግ ነው፡፡ ይሄ ደረጃ መጠይቅ የሚያስነሳ ነው፡፡ የወደድነውና እና የቻልነው የሥራ ዘርፍ በማህበረሰቡ ተፈላጊ ነው እንዴ? ገበያ አለው ወይ? ተስፋ ሰጪነት ምን ያክል ነው? ስንል ትርፋማነቱንና አዋጭነቱን ጥያቄ ምልክት ውስጥ አስገብቶ መመልከት ተገቢ እንደሆነ የሚያመላክት ነው፡፡ ሥራ ፈጣሪነት አምርቂ እና ተስፋ ሰጪ ሆኖ እንዲቀጥል የማህበረሰቡን ጥያቄ መመለስና የብዙሃኑን ፍላጎት የሚነካ መሆን አለበት፡፡ መፈለግ የሚለው ሕግም ከዚህ ጋር የተሰናሰለ ነው፡፡

የመጨረሻ ሆኖ የተቀመጠው መሸጥ ነው፡፡ የሁሉም የሥራ ፈጣሪዎች የመጨረሻ ግብ ውጤት ተኮር ፍጻሜ ነው፡፡ ወደን፣ ችለንና አስፈላጊነቱን አጢነን ማረፊያችን ሊሆን የሚችለው ውጤት ነው። ውጤት ደግሞ ከመሸጥ፣ ከመለወጥ፣ ከመገብየት የሚነሳ ነው፡፡ ሃሳባችን እኚህን ደረጃዎች አልፎ መጨረሻ የሆነው የትርፍ ደረጃ ላይ ሲደርስ ነው አንድ ሥራ ፈጣሪ ተሳካለት የሚባለው፡፡ መሸጥ ገንዘብ ከማምጣትና ትርፍ ከማግኘት ጋር የሚገናኝ ነው፡፡ ሃሳባችን ዳብሮና ጠንክሮ ገንዘብ ሊያመጣልን ከቻለ ስኬታማዎች ነን፡፡

ከላይ በተነሳንባቸው የባለሙያዎች የስታርትአፕ የሥራ ፈጣሪዎች የስኬት ሕጎች በመንተራስ ወጣቱ ሃሳቡን እንዲወድ፣ መቻሉን እንዲያምንና ተፈላጊነቱን እንዲያጤን በስተመጨረሻም ገንዘብ ሊያመጣለት የሚችል መሆኑን መፈተሽ ይኖርበታል፡፡ ባለሙያዎቹ የትኛውም ባለሃሳብ በስታርት አፕ ስም ወደ ሥራ ፈጣሪነት ሲያዘግም በነዚህ የ“መ “መርሆዎች ሥር ራሱን ቢያስቀምጥ መልካም እንደሆነ ይመክራሉ፡፡

ኢትዮጵያ ሀገራችን የሥራና የሥራ ፈጣሪዎች መፍለቂያ እንድትሆን በመንግሥት በኩል ለዘርፉ የተሰጠው ልዩ አትኩሮት መጪውን ጊዜ ብሩህ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ በሃሳብ ማሸነፍ፣ በሃሳብ መበለጥ ባጠቃላይ ለሃሳብ ልዕልና ቅድሚያ የሚሰጥን ምህዳር በመፍጠር የተሳካ ሚና ይጫወታል፡፡ እንደ ጅማሮ በርካታ ተስፋዎች እየታዩበት ነው፡፡

ከላቀ ሃሳብ ውጪ ዋጋ እንዳይኖረን የሆንን ሀገርና ሕዝብ ነን፡፡ ለውጥ ሃሳብን ታኮ፣ ትጋትን ተመርኩዞ በላቁ አእምሮና ልቦች በኩል የሚንጸባረቅ እንደሆነ፣ ዘመናዊነትና ስልጣኔ በራስ አቅም፣ በራስ ተፈጥሮ ወደሌሎች መፍሰስ እንደሆነ፣ ምቹና ቀና ሕግና ደንቦች ለመጪው ትጋት፣ ላለው ተስፋ በመሆን ሀገርን የሚያጅቡ እንደሆኑ በሁሉም ዘንድ ይታመናሉ፡፡ ሃሳቦቻችንን ወደሥራ ለውጠን ከግለሰብ ወደ ማህበረሰብ፣ ከሀገር ወደ አህጉር እንድንሰፋ ስታርት አፕ ጥሩ አጋጣሚ ስለሆነ በእድሉ ተጠቃሚ መሆን ይገባል፡፡

የዓለም ዝማኔ በሃሳብ መበላለጥ የመጣ ነው። ሃሳብ ያለው ወጣት ወደ ልማት እንጂ ወደ ጥፋት አይገባም፡፡ እጆቹን በሥራ አእምሮውን በሃሳብ ያፈረጠመ ወጣት ከምንም በላይ ያስፈልገናል። የጦርነት ታሪኮቻችንን በዚህ መንገድ ካልሆነ አንሻገራቸውም፡፡ ወጣቱ እንዲያስብ፣ እንዲያሰላስል፣ በተመቸና ወደኋላ በማይመልስ ሥርዓት በኩል ወደፊት እንዲገሰግስ መንገድ ሊሰጠው ይገባል፡፡

በሃሳብ ካልሰፋን በምንም አንሰፋም፡፡ ሥርዓቶቻችንን ለሃሳባውያን ቀና ማድረጋችን ለለውጥ ያለንን ቁርጠኝነት የሚያሳይ ነው። ወጣቱን በልማት አሰማርተን መጪውን ጊዜ መጠበቁ ከውሳኔዎቻችን ሁሉ ምርጡ ውሳኔ ሆኖ የሚጠራ ነው፡፡ ሃሳብ፣ ኃይል፣ ትጋትና ቁርጠኝነት በአንድ ላይ የሚገኙት ወጣቱ ጋ ነው፡፡ ለወጣቱ መንገድ አለመስጠት ማለት በእነዚህ እድሎች አለመጠቀም ነው፡፡

ለወጣቱ እንዲሆኑ መንገዶቻችንን እንክፈት። ሥርዓቶቻችንን እንመርምር፡፡ ሕጎቻችንን እናሻሽል፡፡ መንግሥት በዲጂታል ቴክኖሎጂ የዳበረች ኢትዮጵያን በመፍጠር ትጋት ላይ ነው። ስታርት አፕ ደግሞ መነሻው ሃሳብና ቴክኖሎጂ ነው፡፡ ሃሳብን ከቴክኖሎጂ ጋር ያስተሳሰረ ወጣት ደግሞ በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ ዓይነት አላማ ያለው ነው፡፡ በአንድ በኩል ራሱን ይጠቅማል በሌላ በኩል ሥራ ፈጣሪነትን ከቴክኖሎጂ ጋር በማቆራኘት መንግሥት ለያዘው የዲጅታላይዜሽን ተልዕኮ መንገድ ጠራጊ ይሆናል፡፡

ኢኮኖሚ

# ንግድና ግብይት

# የበዓል ገበያው የተለያዩ አማራጮች

**ፍሬሕይወት አወቀ**

በክርስትና ዕምነት ተከታዮች ዘንድ በድምቀት ከሚከበሩ በዓላት መካከል የትንሳኤ /የፋሲካ/ በዓል አንዱ ነው:: ይህ ታላቅ በዓል ሊከበር ጥቂት ቀናት ብቻ ቀርተውታል::

የበዓሉን መቃረብ የሚያመለክቱ በርካታ ሁነቶች መታየት ጀምረዋል:: በአዲስ አበባ ያለው ሁኔታ እንደሚያመለክተው፤ ገበያው መሟቅ ጀምሯል:: የምግብ ሸቀጦች በዓይነት በዓይነቱ በብዛት በገበያው መታየት የጀመሩ ሲሆን፣ ምርቶቹ በከተማዋ በአራቱም አቅጣጫዎች እየገቡ የእሁድ ገበያን ጨምሮ በተለያዩ የገበያ ማዕከላት የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶቹ በስፋት እየቀረቡ ናቸው::

መንግሥት እንደ ሀገር እየታየ ያለውን የኑሮ ውድነት ለማርገብና ገበያውን ለማረጋጋት የተለያዩ ሥራዎችን እንደሚሰራ ይታወቃል:: የዋጋ ንረቱን ለማርገብ የተለያዩ የገበያ አማራጮችን በማዘጋጀት የግብርናና ኢንዱስትሪ ምርቶች ለሕዝቡ ተደራሽ ሲያደርግ ቆይቷል::

ምርቶቹ ለሕዝቡ ተደራሽ ከሚደርጉባቸው ገበያዎች መካከል የእሁድ ገበያ አንዱ ነው:: በእሁድ ገበያ የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶች ለከተማው ነዋሪ በተመጣጣኝ ዋጋ እንደሚቀርብ ይታወቃል:: ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ከእሁድ ገበያዎች በተጨማሪ በተለያዩ አካባቢዎች የግብርና ምርቶች መሸጫ ማዕከላትን በማቋቋም አምራቾች ምርቶቻቸውን በቀጥታ ለሸማቹ ማቅረብ እንዲችሉ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል::

ይህም ሸማቹ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ መሸመት እንዲችልና የኑሮ ውድነቱ የሚያደርስበት ጫና እንዲቀልለት ትልቅ ድርሻ አለው:: በተለይ በበዓል ወቅት ያለውን ፍላጎት ምክንያት በማድረግ የሸቀጦችን ዋጋ ከሚያንሩ ስግብግብ ነጋዴዎች ሸማቹን ለመታደግ መሰል ሥራዎች በስፋት እየተሠሩ ነው:: ከሰሞኑንም መጣሁ መጣሁ ለሚለው የፋሲካ በዓል ሸማቹ የተለያዩ የምግብ ሸቀጦችን ባገኘው የገበያ አማራጭ ያለ ምንም ችግር መሸመት እንዲችል ከተማ አስተዳደሩ በየአቅጣጫው እየተንቀሳቀሰ ይገኛል::

ከገበያ አማራጮቹ መካከል ስድስት ኪሎ አንበሳ ግቢ አጠገብ የግብርና ምርቶች የቀረበበት የበረከት ገበሬዋ ሱቅ አንዱ ነው:: እዚህ ሱቅ ሽንኩርትን ጨምሮ የተለያዩ የአትክልትና የፍራፍሬ ምርቶች በአርሶ አደሩ ዋጋ ቀርበዋል:: በዚሁ ሱቅ ሽንኩርት ስትገዛ ያገኘናት የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ ወይዘሪት ወርቄ ጣሰው መኖሪያዋ ጀሞ አካባቢ ቢሆንም የሥራ ቦታዋ ስድስት ኪሎ በመሆኑ ከበረከት ገበሬዋ ሱቅ የመሸመት አጋጣሚን አግኝታለች:: ለሥራ በወጣችበት አጋጣሚ ወደ ግዥ የገባቸው ዋጋው ቅናሽ በመሆኑ ነው::

በሱቁ ሁሉም ዓይነት የግብርና ምርቶች አሉ:: ዋጋቸውም ተመጣጣኝ በመሆኑ ተመራጭ ናቸው ያለችው ወይዘሪት ወርቄ፣ እሁድ ገበያ አንድ ኪሎ ሽንኩርት ከ50 እስከ 55 ብር ይሸጣል፤ እዚህ ግን አንድ ኪሎ ሽንኩርት 38 ብር ነው ስትል ገልጻለች። ሌሎች ካሮት፣ ጥቅል ጎመን፣ ድንች የመሳሰሉትም የተወሰነ ቅናሽ እንዳላቸው ጠቅሳ፣ ገበያው ለዚህ አካባቢ ነዋሪ ተመራጭ ነው ብላለች::

እሷ እንዳለችው፤ በተለይም ሽንኩርት ለበዓሉ እጅግ አስፈላጊ እንደመሆኑ ከእሁድ ገበያ በተጨማሪ በዚህ መንገድ መቅረቡ በጣም ጥሩ ነው:: ሸማቹ ባመቸው መንገድ መግዛት እንዲችል ያደርገዋል:: አምራቹ በቀጥታ ሸማቹ ዘንድ መድረስ መቻሉ በጣም ጥሩ ነው:: ጥራት ያለው ምርት በተመጣጣኝ ዋጋ መሸመት ያስችለዋል:: ስለዚህ በየአካባቢው እንዲህ ዓይነት የገበያ አማራጭ ቢኖር መልካም ነው:: በማለት አሁን ላይ ምርቶች በስፋት እንደገቡና ዋጋውም ተመጣጣኝ እንደሆነ ገልጻለች::

**በዓሉን አስመልክቶ ምንም ዓይነት የዋጋ ንረት እንዳያጋጥም ምርቶችን ከተለያዩ የሀገሪቷ አካባቢዎች በማምጣት በተመጣጣኝ ዋጋ ለሸማቹ ለማቅረብ እየተሠራ ነው:: ምርቱ በተባለለት ዋጋ ሸማቹ ዘንድ መድረስ እንዲችል በሸማች ህብረት ሥራ ብቻ ሳይሆን በግብረ ኃይል ጭምር ጠንካራ ቁጥጥርና ክትትል እየተደረገ ይገኛል**

እንዲህ ዓይነት የገበያ አማራጮች መስፋታቸው በጣም ጥሩ እንደሆነ የገለጹት ወይዘሮ ጽጌ ረጋሳ በበኩላቸው፣ ከሱቁ ሽንኩርት በ38 ብር፣ ድንች በ28 ብር እና ሌሎች ምርቶችንም እንዲሁ ውጭ ካለው ዋጋ ባነሰ መሸመት እንደቻሉ ተናግረዋል። ከሱቁ በተጨማሪም በአካባቢው የእንቁላል ገበያ መኖሩን ጠቅሰው፤ የአበሻ እንቁላል 11 ብር ፤ የፈረንጅ እንቁላል በስምንት ብር መግዛት እንደቻሉና ገበያው የተሻለ አቅርቦት እንዳለ ነው የጠቆሙት::

ወይዘሮ ጽጌ፤ የሽንኩርት ዋጋ በጣም የናረበት ወቅት እንደነበር አስታውሰው፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ቅናሽ እያሳየ መሆኑ በጣም ጥሩ ነው ሲሉ ገልጸዋል:: በከተማዋ በተለያዩ አካባቢዎች ሽንኩርትን ጨምሮ እንቁላልና ለበዓሉ አስፈላጊ የሆኑ የምግብ ሸቀጦች በስፋት እየታዩ መሆናቸውንም ጠቅሰው፣ ዋጋቸውም ቢሆን ካለፈው የገና በዓል አንጻር ሲታይ በጣም የተሻለ ነው ብለዋል:: ከዚህ ሌላም የዘይት ዋጋ ግን እየጨመረ መምጣቱን ወይዘሮ ጽጌ ጠቅሰው፣ ዘይቱም እንደ ሌላው ምርት ሁሉ ዋጋው ቢስተካከል ጥሩ ነው በማለት ገልጸዋል::

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአትክልትና ፍራፍሬ ዋጋን ለማረጋጋት በከተማዋ የመግቢያ በሮች የገበያ ማዕከላትን ገንብቶ ወደ ሥራ መግባቱ ይታወሳል:: በእነዚህ ማዕከላትም አምራች ገበሬዎችን ጨምሮ ጅምላ አከፋፋዮች የተለያዩ አትክልትና ፍራፍሬዎችን ለሸማቹ በተመጣጣኝ ዋጋ እያቀረቡ ይገኛሉ:: በተለይም በዓሉን አስመልክቶ ምርት በስፋት እንዲቀርብ ከተማ አስተዳደሩ በትኩረት እየሠራ ይገኛል::

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ህብረት ሥራ ኮሚሽን መጪው የፋሲካ በዓልን አስመልክቶ የምርት እጥረት እንዳይከሰት በተለየ ሁኔታ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ መሆኑን ከሰሞኑ ለጋዜጠኞች በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ አስታውቋል:: የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ህብረት ሥራ ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር አቶ ኃብተይስ ዲሮ እንዳሉት፤ እንደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ህብረት ሥራ ኮሚሽን ከዚህ ቀደምም የገበያ ማረጋጋት ሥራ ሲሰራ ቆይቷል::

በአሁኑ ወቅትም ኮሚሽኑ በዓሉን ምክንያት በማድረግ ለሸማቹ አስፈላጊ የሆኑ የምግብ ሸቀጦችን ለማቅረብ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ሲሰራ ቆይቷል:: ለዚህም አስቀድሞ አቅዶ ሥራውን ሊመራ የሚችል ኮሚቴ በማዋቀር በትኩረት እየተሠራ ነው:: ለበዓሉ አስፈላጊ የሆኑ የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶችን ለሸማቹ ለማቅረብ ከክልሎች ጋር ትስስር በመፍጠር ምርት ወደ ከተማዋ ማስገባት ተጀምሯል:: በተለይም ለበዓሉ እንደ ጤፍ፣ ዱቄት፣ ዘይት፣ የቁም እንስሳት፣ እንቁላልና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ምርቶች ወደ ከተማው እንዲገቡ እየተደረገ ነው::

አብዛኞቹ ምርቶቹ ከኦሮሚያ ክልል በስፋት እየገቡ ሲሆን፤ የቁም እንስሳት ከሰዴታን ጮራ፣ ሎሜ አዳማ፣ ወንጂ ስኳር ፋብሪካ አካባቢ ወደ ከተማዋ እየገባ ይገኛል:: እንቁላል ከከተማ ግብርና ከኤልፎራ እንዲሁም ከተደራጁ ወጣቶች ጭምር በማሰባሰብ ወደ ገበያው እየገባ ነው:: እንቁላልን በሚመለከት ይህ ዘገባ እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ ከአምስት መቶ ሺ በላይ እንቁላሎች ወደ ገበያው ገብተዋል:: በቀጣይ በተለይም ከከተማ ግብርና በስፋት የሚገባ በመሆኑ እጥረት ሳያጋጥም በተመጣጣኝ ዋጋ ለሸማቹ ይቀርባል::

የሥጋን በተመለከተም እንዲሁ በከተማዋ በሚገኙ 246 በሚሆኑ የሸማች ሥጋ ቤቶች በኩል ጥራት ያለው ሥጋ በተመጣጣኝ ዋጋ ለማቅረብ እየተሠራ ነው:: በከተማዋ ከሚገኙ ሥጋ ቤቶች ጋር ትስስር በመፍጠር በሬዎችን ወደ ከተማ የማምጣትና ሥጋ ለሸማቹ ለማቅረብ ዝግጅት ተደርጓል:: ሥጋውን የሸማች ሱቆችና መዝናኛ ክበቦችን ጨምሮ በአጠቃላይ ስምንት መቶ በሚደርሱ የሸማች ሱቆችና መዝናኛ ክበቦች ለማቅረብ ኮሚሽኑ ዝግጅት እያደረገ ነው::

ኮሚሽኑ በዩኒየኖች አማካኝነት ምርቶች በበቂ ሁኔታ መግባት እንዲችሉ እየሠራ ነው ያሉት አቶ ኃብተየስ፤ በተለይም በ246 የሸማች ሥጋ ቤቶች ሥጋ ለማህበረሰቡ ማቅረብ ያለባቸው በምን ያህል ዋጋ ነው የሚለውን ጭምር በማኔጅመንት ተወስኗል ብለዋል:: የአንድ ኪሎ ሥጋ ዋጋ ከ400 እስከ 460 እንደሚሆንም ጠቁመዋል:: ዋጋው የሚወሰነው እንደ በሬው ዋጋ ነው መሆኑን ጠቅሰው፣ ዋጋው ከሉካንዳ ቤቶች ጋር በመነጋገር መስማማት ላይ የተደረሰበት ጉዳይም ነው ብለዋል::

ለበዓሉ በጣም አስፈላጊ የሆኑትን ጤፍ፣ በሬ፣ ሽንኩርት፣ እንቁላልና ሌሎች ግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶችን በማስገባት በቂ ዝግጅት መደረጉን የጠቀሱት አቶ ኃብተየስ፤ ምርት ከማስገባት ባለፈ ምርቱ በትክክል ማህበረሰቡ ዘንድ መድረስ እንዲችልም ኮሚሽኑ የቁጥጥርና የክትትል ሥራ እየሠራ እንደሆነ አስታውቀዋል። ኮሚሽኑ ከምርት አቅርቦቱ ጎን ለጎን ለቁጥጥርና ክትትል ሥራውን አቅዶ እየሠራ መሆኑን ጠቅሰው፣ ለዚህም እስካሁን ባለው ዝግጁነት ለበዓሉ የሚያስፈልጉ ምርቶችን ለማቅረብ በቂ ዝግጅት መደረጉን አመላክተዋል::

አቅርቦት ላይ እጥረት እንዳይፈጠር በሚል ኮሚሽኑ አስቀድሞ ፍላጎት መሰብሰቡን ተናግረው፣ ከየክፍለ ከተሞች በተሰበሰብ ፍላጎት መሠረት ምርቶቹ እንደሚቀርቡ ገልጸዋል:: የተሰበሰበውን መረጃ መነሻ በማድረግ አቅምን ባማከለ መንገድ ምርቶችን ለማቅረብ እየተሠራ መሆኑን አስታውቀው፤ ለአብነትም በከተማዋ በሚገኙ የሸማች ህብረት ሥራ ማህበራት ሉካንዳ ቤቶች ብቻ የሚቀርቡ አራት ሺ 610 በሬዎች ፍላጎት መለየቱን አብራርተዋል::

በተመሳሳይም ሌሎች ምርቶችም እንዲሁ በፍላጎት መሠረት እንደሚቀርቡ ተናግረው፣ የአቅርቦት እጥረት እንደማያጋጥም ያላቸውን እምነት ገልጸዋል:: በተለይም ጤፍ በልዩ ሁኔታ በስፋት ወደ ገበያው ማስገባት የተቻለ ሲሆን፤ መጠባበቂያ ጭምር ተዘጋጅቷል ብለዋል:: ለዚህም ባለፉት ሶስት ወራት በልዩ ሁኔታ በከተማ አስተዳደሩ እየተመራ በቂ ምርት እንዲገባ መደረጉን አስታውቀዋል::

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር ህብረት ሥራ ኮሚሽን የሬጉላቶሪ ዘርፍ ምክትል ኮሚሽነር አቶ ተጫነ አዱኛ በበኩላቸው፤ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር ህብረት ሥራ ኮሚሽን በዓሉን አስመልክቶ በርካታ የአቅርቦት ሥራዎችን ሲሰራ መቆየቱን ገልጸዋል:: በተለይም ከምግብ ሸቀጦች ጋር ተያይዞ የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶች ወደ ከተማው እንዲገቡ በርካታ ሥራዎች መከናወናቸውንም አመልክተዋል:: ይህም ህብረተሰቡ በዓሉን በሰላም ማሳለፍ እንዲችልና የኑሮ ጫናውን እንዲያቀልልት እንደሚረዳ ተናግረዋል::

እሳቸው እንዳሉት፤ ማህበረሰቡ በዓሉን በሰላም እንዲያሳልፍና የኑሮ ጫናውን እንዲያቀል ተብሎ የገባው ምርት በተገቢው መንገድ ማህበረሰቡ ዘንድ መድረስ እንዲችል መከታተል ያስፈልጋል:: ለዚህም ከማዕከል እስከ ወረዳ ድረስ ለዚህ ሥራ ቡድን ተደራጅቷል:: ይህ ቡድንም የቀረበው ምርት በትክክል ሕብረተሰቡ ዘንድ መድረሱንና ዋጋዎቹም በሁሉም ህብረት ሥራ ማህበራቱ ተመሳሳይ መሆኑን ለማረጋገጥ የቁጥጥር ሥርዓት ተዘርግቷል::

ይህም በዓሉን በማስመልከት በተገቢውና በተጠናከረ መንገድ እንደ ተቋም የሚሠራ ሲሆን፤ እንደ ከተማ አስተዳደርም ከጸጥታና ሌሎች አካላት ጋር በቅንጅት በልዩ ሁኔታ ይሰራበታል:: በመሆኑም ህብረተሰቡ በዓሉን በሰላምና በተረጋጋ ሁኔታ ማሳለፍ እንዲችል ኮሚሽኑ የበኩሉን ድርሻ ለመወጣት ከፍተኛ ጥረት እያደረገ እንደሆነ አመላክተዋል::

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ህብረት ሥራ ኮሚሽን ለውጥ ላይ ያለ ተቋም መሆኑንና እያደረገ ያለው ሪፎርምም ሁለንተናዊ ሪፎርም ነው ያሉት አቶ ተጫነ፤ ይህም ለተገልጋዩ ምቹና ቀልጣፋ አገልግሎት ለማቅረብ እና ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያስችል እንደሆነ አስታውቀዋል::

እሳቸው እንዳሉት፤ በተለይም በዓሉን አስመልክቶ ምንም ዓይነት የዋጋ ንረት እንዳያጋጥም ምርቶችን ከተለያዩ የሀገሪቷ አካባቢዎች በማምጣት በተመጣጣኝ ዋጋ ለሸማቹ ለማቅረብ እየተሠራ ነው:: ምርቱ በተባለለት ዋጋ ሸማቹ ዘንድ መድረስ እንዲችል በሸማች ህብረት ሥራ ብቻ ሳይሆን በግብረ ኃይል ጭምር ጠንካራ ቁጥጥርና ክትትል እየተደረገ ይገኛል:: ሸማቹ ማንኛውም ዓይነት ችግር ሲያጋጥመው በነፃ የስልክ መስመር 8779 ደውሎ ጥቆማ መስጠት እንደሚችል ገልጸዋል::

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ህብረት ሥራ ኮሚሽን የፋሲካ በዓልን ምክንያት በማድረግ እስከ በዓሉ ዋዜማ ድረስ በአጠቃላይ ከአንድ ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ብር በላይ በሚገመት ገንዘብ የተለያዩ የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶችን በሸማች ህብረት ሥራ ማህበራት በኩል ለሸማቹ እንደሚቀርብ ተመላክቷል::

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## መብት መጠየቅን ያስለመደው የላብ አደሮች ቀን

**ዋለልኝ አየለ**

ነገርየው ዓለም አቀፍ ፖለቲካዊ መልክ የነበረው ነው፡፡ ምንም እንኳን የተጀመረው በአሜሪካና አውሮፓ ሀአገራት እንደነበር ቢነገርም እየቆየ ሲሄድ ግን የሶሻሊስት ሀገራት ንቅናቄ መስሏል፡፡ በእርግጥ ነገሩን ያጧጧፉትም የሶሻሊስት ሀገራት ናቸው፡፡ ብዙ ዝርዝር ምክንያቶች ያሉት ቢሆንም በጥቅሉ ሲታይ ግን፤ የፊውዳል ሥርዓት የድሃ ጉልበት ይበዘብዛል የሚል ነው፡፡ በሀገራችን ዓውድ ስናየው፤ የባላባት ሥርዓት ጭሰኛውን ‹‹እርቦ›› እና ‹‹ሲሶ›› እያሳረሰ ይበዘብዝ ነበር፤ ሠራተኛው የልፋቱን ያህል አያገኝም እንደማለት ነው፡፡ ለዚህም ነው የተማሪዎችን ንቅናቄ አስጀማሪዎች የ60ዎቹ አብዮተኞች ‹‹መሬት ለአራሹ›› የሚል መፈክር ማንሳታቸው፡፡ የላብ አደሮች ቀንም መከበር የጀመረው ንጉሣዊ ሥርዓቱን ባስወገደው የደርግ መንግሥት ነው፡፡

በዓለም አቀፍ ደረጃ ሲታይ ግን የረጅም ጊዜ ታሪክ ያለው ነው፡፡ በአውሮፓ የኢንዱስትሪ መስፋፋትን ተከትሎ የተከሰተ ነው፡፡ ይህ ቀን በአሜሪካ ‹‹የሠራተኛ ቀን (Labor day) በሚል ሲከበር በዓለም አቀፍ ደረጃ ደግሞ ‹‹ሜይ ዴይ (May day›› በሚል ይታወቃል፡፡ ይህም በአውሮፓውያኑ የዘመን ቀመር ግንቦት 1 መሆኑ ነው፡፡ በተለያዩ ፋብሪካዎችና ኢንዱስትሪዎች ውስጥ ያሉ ሠራተኞች መብታቸውን ለማስከበር ያስጀመሩት ንቅናቄ ነው፡፡ በመላው አሜሪካም በመስከረም ወር ይከበራል። እነሆ በኢትዮጵያ ደግሞ በደርግ ዘመነ መንግሥት በደማቁ፣ ከዚያ ወዲህ ደግሞ ቀዝቀዝ ባለ ሁኔታም ቢሆን ይታሰባል፡፡ ሙሉ ታሪኩን ለታሪክ ዓምዳችን እንተወውና ለመሆኑ በአሀገራችን የሠራተኛ መብት ምን ይመስላል? የሚለውን እንታዘብ፡፡

ምንም እንኳን የላብ አደሮች ቀን መከበር ያመጣው ነው ለማለት ባያስደፍርም አሁን ባለው ሁኔታ በኢትዮጵያ ውስጥ የሠራተኛ መብት አይከበርም ለማለት አያስችልም፡፡ ችግሩ ግን በመንግሥት ተቋም ውስጥ ያለው እና በግል የንግድ ቤቶች ውስጥ ያለው ሁኔታ እጅግ የተራራቀ መሆኑ ነው፡፡ በመንግሥት ተቋም ውስጥ ሠራተኛው በሕዝብ በጀት ሲቀልድ፣ በግል የንግድ ተቋማት ውስጥ ደግሞ ባለሀብቶች በድሃ ጉልበት ይጫወታሉ፡፡ በተለይ እንደ አነስተኛ ሆቴሎችና ሬስቶራንቶች፣ መጠጥ ቤቶችና ሌሎች ንግድ ቤቶች ሠራተኞቻቸውን እንዴት እንደሚያደናብሩ በቀላሉ ማንም ሰው የሚታዘበው ነው።

መጀመሪያ በመንግሥት ተቋማት በኩል ያለውን እንመልከት፡፡ የተደራጀ የአሠራር ሕግና ደንብ አለው፡፡ ተቋማቱ የየራሳቸው የሠራተኛ ሕግና ደንብ አላቸው፡፡ ለሁሉም ሠራተኛ የወጣውን የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅም ያከብራሉ፡፡ በጣም አልፎ አልፎ ሕግና ደንቡን የተላለፈ የመንግሥት ተቋም ካለ መክሰስ ይቻላል፤ ከክሱ በላይ የመንግሥት ተቋም ሆኖ ሕግና ደንብን አለማክበሩ ስለሚያስወቅሰው አስቀድሞ ለስሙ ሲል ይጠነቀቃል፡፡ በዋናነት ግን የሠራተኛው መብት በሕግና ደንቡ መሠረት ይከበርለታል፡፡ ለምሳሌ፤ አንዲት ሴት ስትወልድ የሚሰጣት የወሊድ ፈቃድ በመንግሥት ተቋም ውስጥ እና በግል የንግድ ድርጅት ውስጥ እኩል አይደለም፡፡ ይህ መንግሥት ካለበት ሀገራዊ ኃላፊነት አንፃር የሚገርምም ሆን የሚደንቅ ሊሆን አይገባም፡፡

በመንግሥት ተቋም ውስጥ ያለው ልክ ያልሆነ ነገር ግን የሠራተኛ አያያዝ ዝርክርክነት ነው፡፡ መብትን ማክበር እንዳለ ሆኖ፤ የመንግሥትና ሕዝብ ጊዜና ንብረት የሚባክንበት ዝርክርክ አሠራር ግን መብት ማስከበር ሳይሆን ብዝበዛ ነው ሊባል የሚገባው! ለምሳሌ፤ የንብረት አያያዝ ላይ አደገኛ ችግር አለ፡፡ የመንግሥት ንብረት ሲባል የሆነ የባዕድ ንብረት አይነት ተደርጎ ነው የሚታየው፡፡ ይህ የሠራተኛውም የአስተዳዳሪዎችም ችግር ነው፡፡ በእንዲህ አይነት አሠራር የሰዎች የዓመት እረፍትና የወሊድ ፈቃድ ቢከበርም በሕዝብ በጀት የሚገዛ ዕቃ ግን ይባክናል፡፡ በሕዝብ በጀት የሚሠራ የመገልገያ ቦታ (ለምሳሌ መጸዳጃ) በግዴለሽነት ስለሚያዝ በተደጋጋሚ ይበላሻል፣ በተደጋጋሚ ይጠገናል፡፡

በዚህ ሁሉ ውስጥ ለዚያውም የሚዘረፈውን ገንዘብ (ሙስና) ሳንቆጥር ነው፡፡ ከሕግና ደንብ አሠራር ውጭ የሆኑ ወጪዎች ይደረጋሉ የሚባለው ወቀሳ በየመድረኮች የምንሰማው ነው፡፡ ለንብረት መግዣ ወጪ የተደረገ ገንዘብ ተገቢውን ጥራት ያለው ዕቃ ሳይገዛ ገንዘቡን በመቀሸብ (መቀነስ) ለግል ጥቅም ማዋል እና በቀላሉ የሚበላሽ ዕቃ መግዛት በተደጋጋሚ የሚሰማ ወቀሳ ነው። በዚህ ሁኔታ የዘራፊው ሠራተኛ መብት ሲከበር የሕዝብ መብት ግን ተጣሰ ማለት ነው፡፡ ዘራፊው ይህን ስለዘረፍኩ ብሎ ተጨማሪ ሰዓት አይሠራም፡፡

ሌላው በመንግሥት ተቋም ውስጥ ያለው ትልቁ ሀገራዊ ክስረት ‹‹የኔ›› ብሎ የመሥራት ሞራል የሌለ መሆኑ ነው፡፡ በሠለጠኑት ሀገራት የመንግሥት ሠራተኛ በሀገሪቱ ትልቁ የኃላፊነት ስሜት የሚሰማው እና ለሥልጣኔ አርዓያ የሆን ነው፡፡ በሀገራችን ዓውድ ካየነው ግን የመንግሥት ተቋም ውስጥ መቀጠር ‹‹የአርባ ቀን ዕድሌ›› የሚባልባት እየሆን ነው፡፡ እንደ ሀገራዊ አገልጋይነት አይታይም። በኃላፊነት ላይ ያሉትም በግል ጥቅም የሚታሙ ናቸው።መብቱን ብቻ ሲያሳድድ ግዴታዎቹን ግን አይወጣም፡፡ ለመብቱ የሚታገለውን ያህል ግዴታዎቹን ሲጥስ ግን ልብ አይለውም፡፡ ስለዚህ መብትም ይከበር፣ ግዴታም ይከበር፡፡

የሠራተኛ መብት በከፍተና ሁኔታ የሚጣሰው እና ኢ-ሠብዓዊ የሆነ ድርጊት የሚፈጸመው በግል ንግድ ቤቶች ነው፡፡ የግል ንግድ ቤት ባለቤቶች ‹‹በገዛ ንብረቴ!›› የሚሉት የስግብግብነት ሞራለ ቢስ ባህሪ አላቸው፡፡ በጣም ሲከፉ አሰርተው ገንዘብ የሚከለክሉ ሁሉ አሉ። የእሱ ንብረት መግዣ አንድ ሳንቲም እንዳይጎድል ወር ሙሉ ሲለፋ የነበረ ሠራተኛ የዕለት ጉርሱን የሚያገኝበትን ገንዘብ እንዳያገኝ ይራዘምበታል፤ ሲከፋ ደግሞ ጭራሹንም ይከለከላል፡፡ የሁለትና ሦስት ወር አዘግይቶ መክፈል በተደጋጋሚ ከብዙ ሠራተኞች የምንሰማው ቅሬታ ነው፡፡ ባለሀብቱ ለተሻለ ትርፍ የዕቃ መግዣ ካጠረው የዕለት ጉርስ የሌላቸው ሠራተኞች እርሱ ‹‹አሁን ተርፎኛል›› እስከሚል ድረስ መጠበቅ አለባቸው፡፡ ህሊና እና ይሉኝታ፣ ሠብዓዊነት ከሌለ ደግሞ መቼም ቢሆን ገንዘብ ‹‹አሁን ተርፎኛል›› ሊባል አይችልም፡፡

የሠራተኛን ጉልበት ስለሚበዘብዙት እያወራን ስለሆነ እንጂ ከደሞዙ በላይ ትርፍ ጨምረው (ጉርሻ ይሉታል) የሚሰጡ መኖራቸውን አልዘነጋነውም፡፡ ሠራተኛው ከተቀጠረበት ውል ውጭ ሌሎች ወጪዎቹን የሚሸፍኑለት አሰሪዎች እንዳሉ እናምናለን፡፡ በቅርበት የማውቀውን አንድ ምሳሌ ብቻ ልጥቀስ፡፡ በአንድ የግል ባለሀብት ንግድ ቤት ውስጥ ተቀጥሮ ይሠራ የነበረ አብሮ አደግ ጓደኛዬ ከሁለት ዓመት በፊት ሲያገባ ያሠራው የነበረው ባለሀብት 30 ሺህ ብር ሰጥቶት በወቅቱ ብዙ አመስገነናል፡፡ ደሞዝ የሚከለክሉ እንዳሉ ሁሉ እንዲህ አይነቶችም አሉ ለካ ብለን ተገርመናል፡፡ ያንን ብር የሰጠው ብድር አይደለም! ‹‹ለዚህ ቁም ነገር ከበቃህ!›› ብሎ በሰዋዊነት ነው፡፡ ይህ አንድ ነጠላ ምሳሌ ነው፤ የዚህ አይነት ብዙዎች አሉ፡፡

እንደዚህ ማገዙ ቢቀር እንኳን (የሕግ አስገዳጅነት ስለሌለው) ሕግ እየጣሱ የሠራተኛ ደሞዝ የሚከለክሉ፣ የደሞዝ ቀን ሲደርስ ሰበብ አስባብ ፈልገው የሚያባርሩ ሕግንም፣ ሞራልንም ሊፈሩ ይገባል!

# ዓለም አቀፍ

## ቻይና ሃማስና ፋታህን ማደራደር ጀመረች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ቻይና የፍልስጤም ተቀናቃኝ ቡድኖች የሆኑትን ሃማስ እና ፋታህ ማደራደር ጀመረች፡፡

የሁለቱ ቡድኖች ተወካዮች በቤጂንግ ያደረጉት የመጀመሪያው ንግግር “ተስፋ ሰጪ” ውጤት የታየበት መሆኑንም የቻይና የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ ሊ ጂያን ተናግረዋል።

ቃልአቀባዩ በዕለታዊ ጋዜጣዊ መግለጫቸው ዝርዝር ጉዳዮችን ባይጠቅሱም፤ የሃማስና ፋታህ ተወካዮች በቻይና ጋባዥነት ቤጂንግ በመገኘት ልዩነታቸውን ለማጥበብ ጥልቅ ውይይት ማድረጋቸውን ገልጸዋል።

“ሁለቱም አካላት የፍልስጤማውያንን አንድነት ለማረጋገጥና ጥምረት ለመፍጠር ተከታታይ ውይይቶችን ለማድረግ ተስማምተዋል” ም ነው ያሉት። ቤጂንግ የፍልስጤማውያንን ውስጣዊ አንድነት ለማጠናከርና የረጅም ጊዜ ነጻ ሀገር የመመሥረት ጥያቄ ምላሽ እንዲያገኝ የምታደርገው ጥረት በሃማስም ሆነ በፋታህ ተወካዮች መደነቁን መግለጻቸውንም አሶሼትድ ፕሬስ ዘግቧል።

ለእስራኤል ነጻ ሀገርነት እውቅና መስጠት የማይፈልገውና በስድስት ቀናቱ ጦርነት በእስራኤል በሃይል የተያዙ ቦታዎች ተለቀው ነጻዋ ፍልስጤም ትመሠረታለች የሚለው ሃማስ ከእስራኤል ጋር የሰላም ስምምነት ከተፈራረመው የማህሙድ አባሱ ፋታህ ጋር ግንኙነቱ የሻከረ ነው።

በተለይ በፈረንጆቹ 2006 በተካሄደው ምርጫ ሃማስ ማሸነፉን ተከትሎም ዌስትባንክን ከሚያስተዳድረውና ፋታህ ከተቆጣጠረው የፍልስጤም አስተዳደር ጋር ልዩነቱ መስፋቱ ይታወሳል።

ሁለቱ ቡድኖች ተከታታይ ድርድር አድርገው የአንድነት መንግሥት ለመመስረት መስማማታቸውም አይዘነጋም።

ስምምነቱ ሃማስ የፍልስጤም አስተዳደር ከእስ



ራኤል ጋር የደረሰውን የሰላም ስምምነት እንዲያከብር የሚያደርግ ቢሆንም ለእስራኤል ሉዓላዊ ሀገርነት እውቅና ያልሰጠበት በመሆኑ እስራኤልና አሜሪካ የአንድነት መንግሥቱን እውቅና አንሰጠውም ብለው ኢኮኖሚያዊ ማዕቀቦችን ጥለው ነበር።

ይህም የሃማስና ፋታህ የአንድነት መንግሥት በአጭር ጊዜ እንዲፈርስና ግጭት እንዲቀሰቀስ ምክንያት መሆኑ ይታወሳል።

እስራኤልና ምዕራባውያን አጋሮቿ ሃማስን በሽብርተኝነት በመፈረጅ ዌስትባንክን ለሚያስተ ዳድረው ፋታህ ደግሞ ዓለምአቀፍ እውቅና በመስጠት የፍልስጤም የነጻነት ትግልን በሁለት ጎራ እንደከፈሉት ይነገራል።

ሰባተኛ ወሩን በያዘው የጋዛ ጦርነት አሜሪካና ሌሎች ምዕራባውያን ሀገራት ለቴል አቪቭ የሚያደርጉት ወታደራዊ ድጋፍ በፍልስጤማውያን ላይ እያደረሰ ያለውን ጉዳት ስትኮንን የቆየችው ቻይና ለፍልስጤም ነጻ ሀገርነት እውቅና ትሰጣለች።

የፍልስጤም ተቀናቃኝ ሃይሎችን በማደራደር የመካከለኛው ምስራቅ ፖለቲካ በምዕራባውያን ብቻ መዘወሩ ሊያበቃለት ይገባል ብላለች።

ቤጂንግ ባለፈው ዓመት ሳኡዲ አረቢያ እና ኢራንን በማደራደር ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነታቸውን ዳግም እንዲጀምሩ ያደረገችው ስኬታማ ጥረትም ሁነኛ ማሳያ ነው።

## የሀውቲ ታጣቂዎች በቀይ ባህር እና ህንድ ውቅያኖስ በአራት መርከቦች ላይ ጥቃት አደረሱ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የሀውቲ ታጣቂዎች በቀይ ባህር እና ህንድ ውቅያኖስ በአራት መርከቦች ላይ ጥቃት አድርሰዋል።

የሀውቲ ታጣቂዎች በህንድ ውቅያኖስ ላይ ስትጓዝ የነበረችውን ኤምኤስሲ ኦሪዎን እቃ ጫኝ መርከብን በድሮን ማጥቃታቸውን ሮይተርስ ዘግቧል።

ይህ ጥቃት የሀውቲ ታጣቂዎች ከእስራኤል ጋር እየተዋጋ ላለው የፍልስጤሙ ታጣቂ ቡድን ሀማስ አጋርነት ለማሳየት በሚል በዓለምአቀፍ የመርከብ እንቅስቃሴ ላይ እያደረሱ ያሉት የጥቃት ዘመቻ አካል ነው ተብሏል።

የኤልኤስኢጂ መረጃ እንደሚያመለክተው ከሆነ የፖርቹጋል ሰንደቅ ዓላማ ስታውለበልብ የነበረችው



ኤምኤስሲ ኦሪዎን መርከብ ከፖርቹጋሉ ሲነስ ወደብ ኦማን ወደሚገኘው ሰለላህ ወደብ እየተጓዘች ነበር።

መርከቧን በባለቤትነት የሚያስተዳድራት ዞዲያክ የተባለው ማሪታይም ኩባንያ ነው። እስራኤላዊው ባለሀብት ኢያል ኦፈር ከዚህ ኩባንያ ድርሻ እንዳለው ይገለጻል።

በኢራን የሚደገፉት የሀውቲ ታጣቂዎቹ ከባለፈው ህዳር ወር ወዲህ በቀይ ባህር፣ በኤደን ባህረ ሰላጤ፣ በባብኤል ማንዴብ የባህር ወሽመጥ ተደጋጋሚ የድሮን እና የሚሳኤል ጥቃት በማድረስ የመርከብ ኩባንያዎች መስመር እንዲቀይሩ እና ለከፍተኛ ወጪ እንዲዳረጉ አስገድደዋል።

ባለፈው መጋቢት የሀውቲ ቡድን መሪ ከእስራኤል ጋር ግንኙነት ያላቸው መርከቦች በህንድ ውቅያኖስ በኩል እንዳያልፉ የሚያደርሱትን ጥቃት እንደሚያሰፉ ገልጾ ነበር።

የቡድኑ መሪ በትናንትናው ዕለት በቴሌቪዥን ባስተላለፈው መልእክት እንዳስታወቀው፤ በቀይ ባህር ሳይክላድስ የንግድ መርከብን እና በሁለት የአሜሪካ ዲስትሮየርስን አጥቅቷል። የእንግሊዝ ማሪታይም ሴኩሪቲ ኩባንያም የማልታ ሰንደቅ ዓላማ የምታውለበልብ ከጅቡቲ ወደ ሳኡዲ አረቢያ ጅዳ ስትጓዝ የነበረች መርከብ ሰኞ እለት ጥቃት እንደደረሰባት ቀደም ብሎ ሪፖርት አድርጓል።

አሜሪካ እና እንግሊዝ የሀውቲ ታጣቂዎችን ለመበቀል በይዞታቸው ላይ ተደጋጋሚ ጥቃት እያካሄዱ ናቸው።

ዜና

# ዕድሮች ቀብር ከማስፈጸም ባሻገር የአባሎቻቸውን ችግር ሊፈቱ ይገባል

ዮርዳኖስ ፍቅሩ

አዲስ አበባ፡- ዕድሮች ቀብር ከማስፈጸም ባሻገር የአባሎቻቸውን ችግር ፈቺ ሊሆኑ እንደሚገባ ተገለጸ።

የዕድሮች ሚና፣ አደረጃጀትና ያሉባቸው ተግዳሮቶች ላይ ትኩረቱን ያደረገ ጥናት በትናንትናው ዕለት ቀርቧል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሴቶች ሕፃናትና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ እና በኮተቤ ትምህርት ዩኒቨርሲቲ ትብብር የተጠናው ጥናት ዕድሮች አሠራራቸውን እንዲያዘምኑና ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ተሳትፏቸውን እንዲያሳድጉ በምን መልኩ ሊታገዙ እንደሚገባ ማመላከትን ዓላማው ያደረገ መሆኑ በመድረኩ ተገልጿል፡፡

የሴቶች ሕፃናትና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ ምክትል ኃላፊ ወይዘሮ ገነት ቅጣው፣ ቢሮው በከተማው በማህበራዊ ዘርፍ ያሉ አደረጃጀቶችን የመደገፍ ግዴታ የተጣለበት እንደመሆኑ ጥናቱ እንዲጠና ማድረጉን አስታውቀዋል።

ዕድሮች ቀደመትና ሰፊ የሰው ኃይል ያላቸው አደረጃጀቶች የመሆናቸውን ያህል ማኅበራዊ ሚናቸው አናሳ መሆኑን ያነሱት ኃላፊዋ ፤ጥናቱ የዕድሮችን ሚና ለማሳደግ ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል ብለዋል፡፡

ጥናቱ አሁን ላይ ከባለድርሻ አካላት ይቅረብ እንጂ ዩኒቨርሲቲው አጠናቆ ለቢሮው ያስረከበው ከሁለት ዓመት በፊት መሆኑንም ተናግረዋል፡፡

ቢሮው በጥናቱ የቀረቡ ምክረ ሃሳቦችን ወደ ተግባር በመቀየር ሂደት ላይ መሆኑን ያነሱት ወይዘሮ ገነት፣ በመንግሥትና በዕድሮች መካከል ያለውን ግንኙነት ሥርዓት ለማበጀት የሚረዳ መመሪያ አጽድቆ ወደ ተግባር መቀየሩንም አስታውቀዋል፡፡

ጥናቱን ያቀረቡት በኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ የአስተዳደርና ልማት ምክትል ፕሬዚዳንትና የጥናቱ አስተባባሪ ሽመልስ ዘውዴ (ዶ/ር) እንዳሉት፣ ጥናቱ ረዥም ጊዜ የወሰደና በጥልቀት የተሠራ ነው፡፡

የዕድሮች ኋላ ቀር የመረጃ አያያዝን መከተላቸው፣ ማኅበራዊ ተሳትፏቸው አናሳ መሆኑና ለቅሶ ላይ ብቻ ከማተኮር ባለፈ አባሎቻቸውን መደገፍ ላይ ከፍተኛ ድክመት እንዳለባቸው ጥናቱ ማመላከቱን ሽመልስ (ዶ/ር) አንስተዋል፡፡

ዩኒቨርሲቲው ዕድሮች ያሉባቸውን ችግሮች በዝርዝር የለየ የጥናት ግኝትን ጨምሮ፣ በአዲስ አበባ የሚገኙ ዕድሮችን የተ።መለከቱ ዝርዝር መረጃዎችን በማጠናቀር ለቢሮው ማስረከቡንም አስታውቀዋል፡፡

ጥናቱ የዕድሮችን የገንዘብና መረጃ አያያዝና አጠቃላይ አሠራሮችን በተመለከተ ዕድሮች ሥልጠና እንደሚያስፈልጋቸው ማመላከቱን አንስተው፣ ዩኒቨርሲቲው በጥናቱ የደረሰበትን ግኝት መነሻ ያደረገ የሥልጠና መመሪያ አዘጋጅቶ ለቢሮው የሰጠ መሆኑን ሽመልስ (ዶ/ር) ተናግረዋል፡፡

እርሳቸው እንዳሉት፣ በጥናቱ ዕድሮችንና መንግሥትን ሊገዛ የሚችል የሕግ ማዕቀፍ ሊኖር እንደሚገባ ምክረ ሃሳብ የቀረበ ሲሆን፣ ቢሮው ይህን ምክረ ሃሳብ መነሻ ያደረገ መመሪያ አዘጋጅቶ ተግባር ላይ አውሏል፡፡

መመሪያው ተግባር ላይ መዋሉ ዕድሮች ሕጋዊ ሰውነት እንዲኖራቸውና ኃላፊነታቸውን አውቀው ሥራቸውን እንዲሠሩ ብሎም በየትኛውም ተቋም ዘንድ ተቀባይነት የሚያገኙበትን ዕድል የሚፈጥርላቸው ነው።

በመድረኩ የተገኙ የዕድር አመራሮችና አባላት በበኩላቸው፣ ዕድሮችን መደገፍን ታሳቢ አድርጎ ጥናቱ እንዲካሄድ በማድረጉ አመስግነው፣ በዕድሮችና በመንግሥት መካከል ሥርዓት የተበጀለት ግንኙነት እንዲኖር መመሪያ ተግባር ላይ የመዋሉ ተገቢነት ላይ አስምረዋል፡፡

ዕድሮች አባሎቻቸውን ለመደገፍ ያላቸውን ፍላጎት የገለጹ ሲሆን፣ ጥናቱን መነሻ አድርጎ ሥራ ላይ የዋለው መመሪያን ኢኮኖሚያዊ አቅማቸውን ለማጎልበትና የልማት ተሳታፊነታቸውን ለማሳደግ ይረዳል ብለዋል፡፡

በቀጣይም መንግሥት የሀገር እሴት የሆነውን ዕድር የበለጠ በማጠናከር ሂደት አጋርነቱን አጠናክሮ እንዲቀጥል ጠይቀዋል፡፡

በመድረኩ ጥናቱን ላካሔደው የኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲና መምህራን ምስጋና ቀርቧል።

## አዲስ አበባን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በመዲናዋ እየተሰሩ የሚገኙት የኮሪደር ልማቶች፣ መንገዶች እና የወንዝ ዳር ፕሮጀክቶች የአፍሪካ ከተማ ብቻ ሳትሆን ዓለም አቀፍ ከተማ እንድትሆን ደረጃዋን ያሻሽላሉ ሲሉም አስረድተዋል፡፡

ከሌሎች የዓለም ሀገራት አንጻር እንኳን ስንመለከት መንገድ የሌለው ከተማ ቀጭጮ ነው የሚቀረው ያሉት ነዋሪው፤ የኮሪደር ልማቱ ለንግድ እና ለመዝናኛ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ ለከተማዋ ነዋሪም ሳቢ አካባቢን ይፈጥራል፡፡ በዚሁ ልክም የሥራ ዕድል እንደሚፈጥር አስተያየታቸውን ሰጥተውናል፡፡

አራት ኪሎ ሥላሴ ቤተክርስቲያን አካባቢ ነዋሪ የሆኑት ወይዘሮ ጽጌ ኃይሌ በበኩላቸው፤ ሌላ ሀገር አይቶ ለመጣ ሰው እየተሠራ ያለው ሥራ በጣም ደስ የሚል እና ሀገሬ አማረባት ብሎ ደፍሮ ለመናገር የሚያስችል ነው ይላሉ ፡፡

ልማቱ የሚደገፍና በነጻነት የአካባቢውን ውበት እያደነቁ ለመንቀሳቀስ ያስችላል ያሉት ወይዘሮ ጽጌ፤ የልማት ተነሺ እንደመሆናችን የሚሰጠን ተለዋጭ ቦታ ከኖርንበት አካባቢ ብዙ ባይርቅ ጥሩ ነው ሲሉ ሃሳባቸውን ሰጥተዋል፡፡

አራት ኪሎ አካባቢ አርመን ህንጻ ነዋሪ የሆኑት ሰለሞን አሊ(ዶ/ር) በበኩላቸው፤ የልማት ሥራው ከቱሪዝም እና ከኢኮኖሚ ጠቀሜታው ባሻገር ሕዝቡ በምቹና ማራኪ በሆነ አካባቢ እንዲኖር የሚያስችል ነው ። ዘመናዊ መሠረተ ልማቶች የተሟሉለት ከተማ ለማድረግ ያስችላል፡፡ ከዚህ አኳያ የኮሪደር ልማቱ የሚደገፍና ይበል የሚያሰኝ ነው ይላሉ፡፡

40 እና 50 ዓመት አብረው የኖሯቸው ጎረቤቶቻቸው ወደ ሌላ ቦታ ተዛውረው የተሻለ ቤት እንደተሰጣቸው የገለጹት ነዋሪው፤ ወደፊትም እንደዚህ አይነት ልማቶች ሕዝቡን በጥልቀት በማማከርና በማሳተፍ ሊቀጥሉ ይገባል ነው ያሉት፡፡

የአራት ኪሎ አካባቢ ነዋሪ የሆኑት አቶ ማስረሻ ታደሰ በበኩላቸው፤ አንድ ከተማ ሁልጊዜም በተመሳሳይ ሁኔታ መቀጠል የለበትም፡፡ አዲሱ ትውልድ በየጊዜው አዳዲስ ነገሮችን እያሻሻለ መሄድ አለበት፡፡ ከዚህ አኳያ እንደማህበረሰብ የልማት ሥራውን እደግፋለው ሲሉ አስረድተዋል፡፡

በተጨማሪም አቶ ማስረሻ፤ ከተማውን በማልማት ሂደት ለሚነሱ ነዋሪዎች ተመጣጣኝ ነገር ቢሰጥ መልካም ነው፡፡ ሥራቸው የመኖሪያ ቦታቸው አካባቢ ለሆኑ ሰዎች እሩቅ ቦታ የሚሄዱ ከሆነ ጫና ስለሚፈጥር በዚህ ረገድ ቢታሰብበት ጥሩ ይሆናል ሲሉ ሃሳባቸውን ሰጥተዋል፡፡

አራት ኪሎ አራዳ ክፍለ ከተማ አካባቢ ነዋሪ የሆኑት አቶ ተክለሃይማኖት አቦሴ የኮሬደር ልማቱ ከተማዋን የማስዋብ፣ መንገዶችን የማስፋትና መሠረተ ልማቶችን የማሻሻል ዓላማ እንዳለው ተመልክተናል፡፡ ይህ መልካም ተሞክሮ በአዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን ወደ ሌሎች የሀገሪቱ ከተሞች ሊስፋፋ ይገባል ነው ያሉት፡፡

የአዲስ አበባ ነዋሪ የሆኑት አቶ ጌታሁን መንገሻ እንደተናገሩት፤ ከዚህ በፊት በአካባቢው የተለያዩ ቆሻሻዎች እንደሚጣሉ በመግለጽ፤ አሁን በመንግሥት የተጀመረው ሥራ ከተማዋን ጹዱና ውብ የሚያደርጋት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ዘላቂ ጤናማ ማህበረሰብ ለመፍጠር ያስችላል ባይ ናቸው፡፡

አዲስ አበባ የአፍሪካ መዲና ሆና ሁሌም በተመሳሳይ ሁኔታ ትቀጥል ማለት የማያስኬድ ነው። ዳሩ ለመቷል አሁን ደግሞ መሀሉ ሊለማ ይገባል ብለዋል፡፡

ከተማ አስተዳደሩ በተለያዩ አካባቢዎች የተሠሩ መሠረተ ልማቶችን ለማገናኘት የሚያስችሉ አምስት የኮሪደር ልማቶችን እየሠራ እንደሆነ ይታወቃል።

ይህም ከዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም እስከ አራት ኪሎ፤ ከመስቀል አደባባይ- ቦሌ ድልድይ፤ ከቦሌ ድልድይ-መገናኛ-ሲኤምሲ-አዲስ አፍሪካ ኤግዚቢሽን እና ኮንቬንሽን ማዕከል፤ ከሜክሲኮ-ሳር ቤት-ወሎ ሰፈር እንዲሁም ከአራት ኪሎ- መገናኛ የኮሪደር ልማቱ አካል መሆኑ ተገልጿል።

## ለዓባይ ግድብ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ግንኙነት ዳይሬክተር አቶ አብርሃም ኃይሉ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ግድቡን ለማጠናቀቅ የሚደረገው ሕዝባዊ ድጋፍ በተለያየ መልኩ ቀጥሏል፡፡

በዘንድሮው በጀት ዓመት በዘጠኝ ወራት አንድ ቢሊዮን 114 ሚሊዮን 883 ሺህ ብር በላይ ለግድቡ ተሰብስቧል ያሉት አቶ አቶ አብርሃም ፤ ገቢውም ከሀገር ውስጥ ቦንድና ስጦታ ፣ የዳያስፖራ ቦንድና ስጦታ እንዲሁም በ8100 የሞባይል አጭር የፅሁፍ መልዕክት አገልግሎት የተሰበሰበ መሆኑን አመላክተዋል።

በዘጠኝ ወሩ በአጠቃላይ ከተሰበሰበው ገቢ ዘጠኝ ሚሊዮን 909 ሺ 39 ብር የሚሆነው ከዳያስፖራው ማህበረሰብ የተሰበሰበ መሆኑ ጠቁመዋል፡፡

የገቢ አሰባሰብ ሂደቱ ከሀምሌ ወር 2015 ዓ.ም እስከ ህዳር ወር 2016 ዓ.ም ያለው የገቢ አሰባሰብ ሁኔታ ከ 2015 ዓ.ም ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር ያነሰ የነበረ ቢሆንም ከታህሳስ እስከ መጋቢት ወር 2016 ዓ.ም የተሻለ የገቢ ማሰባሰቢያ ንቅናቄዎች በመሠራታቸው ጥሩ ውጤት መገኘቱን ተናግረዋል፡፡

የዓባይ ግድብ የተጀመረበት 13ኛ ዓመት በመጋቢት ወር መከበሩን አስመልክቶ የተለያዩ የንቅናቄ መድረኮች መካሄዳቸውን የገለጹት አቶ አብርሃም፤ በወቅቱ 182 ሚሊዮን 899 ሺ 52 ብር መሰብሰብ መቻሉን ገልጸዋል።

በወሩ የተሰበሰበው ገቢም ከ 2015 ዓ.ም ተመሳሳይ ወር ጋር ሲነጻጸር በ87 በመቶ በልጦ የተገኘ ሲሆን፤ የግድቡ ግንባታ ከተጀመረበት 2003 ዓ.ም ጀምሮ እስከ መጋቢት 2016 ዓ.ም ከ ሀገር ውስጥ ቦንድ ሽያጭና ስጦታ ፣ ከዲያስፖራው ማህበረሰብ ቦንድ ሽያጭና ስጦታ እንዲሁም ከልዩ ልዩ ገቢዎች ከ 19 ቢሊዮን 345 ሚሊዮን ብር በላይ መሰብሰብ መቻሉን ዳይሬክተሩ አብራርተዋል።

በግድቡ ድጋፍ አሰባሰብ ላይ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ያቅሙን እያበረከተ መሆኑን አቶ አብርሃም አንስተው፤ ድጋፉ ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባ መልዕክት አስተላልፈዋል።

## የሠራተኛውን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ኮንፌደሬሽን ፕሬዚዳንት አቶ ካሳሁን ፎሎ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ የዘንድሮ የሠራተኞች ቀን የሠራተኛውን የሙያ ደህንነትና ጥቅም በሚያስከብሩ ውይይቶች ይከበራል፡፡

በዓሉ በአዲስ አበባና በዙሪያዋ የሚገኙ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች እና በአዲስ አበባ በኦሮሞ ባህል ማዕከል በፓናል ውይይቶች ተከብሮ ይውላል ያሉ ሲሆን፤ በሌሎች ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ባሉባቸው በመቀሌ፣ በድሬዳዋ፣ ሐዋሳ፣ በአዳማና በጅማ በተመሳሳይ ሁኔታ በውይይት ይከበራል ብለዋል፡፡

የሠራተኞች ቀን ሲከበር ዋና ዋና የሠራተኞች ጥያቄ የሚቀርቡበት ነው ያሉት አቶ ካሳሁን፤ በተለይ ሠራተኛው በኑሮ ውድነት እየተጎዳ በመሆኑ የሥራ ግብር ቅነሳ እንዲሁም ዝቅተኛ የደሞዝ ወለል የሚወስን ቦርድ ተቋቁሞ ውሳኔ እንዲያገኝ ለመንግሥት ጥያቄዎች እየቀረቡ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በተጨማሪም በዓሉ መከበሩ ከዚህ ቀደም የሙያ ደህንነትና ጤንነት ባልተጠበቀ መልኩ ለሚሠሩ ሠራተኞች መብትና ጥቅም ለማስከበር መስዋዕትነት የከፈሉና ተጋድሎ ላደረጉ ሠራተኞች ለመዘከርም ጭምር ነው፡፡

እንደ አቶ ካሳሁን ገለጻ፤ በተለይ ግጭቶች ባሉባቸው አካባቢዎች ሠራተኞች እየተጎዱ በመሆኑ መንግሥት ያሉ ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ የሚፈቱበትን ሁኔታ ማመቻቸት አለበት፡፡

ለመንግሥት የቀረቡ ጥያቄዎች እንዳሉ ጠቅሰውም፤ ለጥያቄዎች አስቸኳይ ምላሽ እንዲሰጣቸው ጠይቀዋል፡፡

በኤጀንሲ የሚሠሩ ሠራተኞች በሀገሪቱ ዝቅተኛ የደሞዝ ወለል ጣሪያ ባለመኖሩ ሠራተኛው ለጉልበት ብዝበዛ እየተዳረገ ነው ያሉት አቶ ካሳሁን፤ ይህንን የሚያስቀር መመሪያ ቢወጣም ተግባራዊ ሳይሆን መቆየቱን ተናግረዋል፡፡

ኮንፌደሬሽኑ ለጉዳዩ ተግባራዊነት ከሚመለከተው አካል ጋር እየሠራ ነው ያሉ ሲሆን፤ የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር መመሪያውን ማውጣት አይችልም ተብሎ ክርክር ቢነሳበትም አሁን በመፈቀዱ የተወሰኑት ላይ ተግባራዊ እየተደረገ እንደሚገኝ አቶ ካሳሁን አብራርተዋል፡፡

## “መላው ሕዝብ ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ክርስቲያን ለንቅናቄው ድጋፍ ትሰጣለች ብለዋል፡፡

በአዲስ አበባ በርካታ የጽዳትና የልማት ሥራዎች እየተሠሩ መሆናቸውን ጠቅሰው፤ የመጸዳጃ ቤቶችን ለመገንባት ለታሰበው ንቅናቄ ቤተ ክርስቲያን ድጋፏን እንደምትሰጥ ገልጸዋል፡፡

በከተሞች የንጽህና ችግር የሚነሳው ከድህነት ሁኔታ ጋር መሆኑን ገልጸው፤ ችግሩን ለመቅረፍ መንግሥት እየሄደበት ያለው መንገድ የሚደገፍ ተግባር መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ንጽህና ጤና እና ሀብት በመሆኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ንጽህናን የሚወድና የሚያከብር መሆኑን በመግለጽ፤ ንቅናቄው በሁሉም ከተሞች የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች ጽዳታቸውን የሚጠብቁበትና ቆሻሻን በተገቢው ሁኔታ የሚያስወግድበት መንገድ ሊመቻች እንደሚገባ አመላክተዋል፡፡

ወጣቶች በፈጠራ ሥራቸው የሚሠሯቸው ተንቀሳቃሽ የጽዳት መገልገያ መሣሪያዎች ሊበረታቱ የሚገባቸው መሆኑን የገለጹት ብፁዕ ካርዲናል አቡነ ብርሃነኢየሱስ፤ የሥራ ፈጠራው በመላው ሀገሪቱ ከተሞች ተግባራዊ በማድረግ ዜጎች የሚገለገሉበትን መንገድ ማመቻቸት ተገቢ ነው ብለዋል፡፡

ቤተ ክርስቲያን ባሏት ተቋማት፣ በትምህርት ቤቶች፣ በህክምና እና ማህበራዊ ማዕከላት ማስተማሯን እንደምትቀጥል ጠቅሰው፤ ንቅናቄው የሚደገፍ ትልቅ ተግባር በመሆኑ የሀገሪቱ ሕዝብ ከተማን ጽዱና ንጹህ ለማድረግ በሚደረገው ሥራ ላይ እንዲተባበር መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ዶ/ር ለሁሉም ምቹ የሆኑ ከተሞችን ለመፍጠር የሚያስችል በጽዱ ጎዳና - ኑሮ በጤና ንቅናቄን ማስጀመራቸው ይታወሳል፡፡

ማህበራዊ

# ባለውለታዎቻችን

## የነፃነት አርበኞቹ የሚያዝያ 27 ጀግኖች

ክብረአብ በላቸው



ኢትዮጵያ በታሪኳ የትኛውንም ሀገር በኃይል ወርራ አታውቅም። ነገር ግን በሀገረ መንግሥት ታሪኳ ውስጥ ብዙዎች ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያንን ለማንበርከክ ያልፈነቀሉት ድንጋይ የለም። እርሷ ደግሞ ለየትኛውም ባዕድ ወራሪ እጅ ሰጥታ አታውቅም። በተለይም አፍሪካን በቅኝ ግዛት ለመቀራመት አውሮፓውያን ተስማምተው ሲዘምቱ፤ ባርነትን አንቀበልም ባሉ በጀግኖቹ ልጆቿ ነፃነቷን አስከብራ እስከዛሬ ዘልቃለች።

ኢትዮጵያ እንደዋዛ የተፈጠረች ሀገር አይደለችም። የዘመናት ውጣ ውረድን ድል አድርገው በመጡ ሕዝቦች የተገነባች ሀገር ናት፡፡ የኢትዮጵያዊነት እሴት መሠረቱ ጽኑ ነው፡፡ አባቶች ደማቸውን እንደ ጅረት አፍሰው ነገን አስበው በደማቸው ያጸኗት ሀገር ናት፡፡ በተለይ በጣሊያን የወረራ ዘመን ኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማዋ ከታጠፈ፣ ሉዓላዊነቷ ከተደፈረ 5 ዓመታት በኋላ ነፃነቷን ያስመለሰችው ከ83 ዓመት በፊት ሚያዝያ 27 ቀን 1933 ዓ.ም ነው፡፡ በዚህ ዘመን ንጉሠ ነገሥቱ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በአርበኞች ብርታትና መስዋዕትነት የጣሊያን ባንዲራ አውርደው የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ በታላቁ ቤተ መንግሥት ሰቀሉ።

የሚያዝያ 27 የንጉሠ ነገሥቱ አዲስ አበባ ገብተው ሰንደቅ ዓለማ መስቀል ሌላው ታሪካዊነቱ ከአምስት ዓመታት አስቀድሞ ሚያዝያ 27 ቀን 1928 በዚያው ቀን ወደ ኢትዮጵያ የዘመተው የጣልያኑ ጦር አዛዥ ጄኔራል ባዶሊዮ አዲስ አበባ ገብቶ በታላቁ ቤተ መንግሥት የጣሊያንን ባንዲራ የሰቀለበት ቀን መሆኑ ነው። ጣሊያን ከዓድዋ ሽንፈቷ 40 ዓመታት በኋላ በዘመናዊ የጦር መሣሪያና በወታደራዊ ኃይል ይበልጥ ደርጅታ ኢትዮጵያን ከሦስት አቅጣጫዎች ወረረች። ከዓድዋው ዘመቻ ያልተሻለ የጦር ትጥቅ የነበራት ኢትዮጵያም የጣሊያንን ጦር በፅናት ተዋጋች።

የወቅቱ ኃያላን እንግሊዝና ፈረንሳይ የጦር መሣሪያ በግዢ እንዳታገኝ ለጣሊያን ተደርበው ስላሴሩባት ኢትዮጵያ ብቻዋን ጦርነቱን በመጋፈጧ ድል ማግኘት አልቻለችም።

የየግንባሮቹ የኢትዮጵያ የጦር አዛዦች ብዙዎቹ ሞተው ሠራዊቱም በመርዝ ጋዝና በአውሮፕላን ቦምብ ተደብድቦ ያለቀው አልቆ የቀረው ቀርቶ ጣልያን ጊዜያዊ ድል አግኝታ ዋና ዋና ከተሞችን ቢቆጣጠርም ኢትዮጵያውያን ጀግኖች በገጠሩ ክፍል እምቢ ለነፃነቴ፣ እምቢ ለሀገሬ ብለው የሽምቅ ውጊያ ጀመሩ።

ንጉሠ ነገሥቱም ስደት ሄደው በጊዜው ለነበረው የመንግሥታቱ ማህበር (ሊግ ኦፍ ኔሽን) አቤቱታ አቀረቡ። የሚሰማቸው ግን አላገኙም። በሌላ በኩል አርበኞች ግን ከቀን ወደ ቀን ድል እየተቀናጁ የጣሊያን ወታደሮችን መፈናፈኛ፤ መግቢያ መውጫ አሳጧቸው። ከጣሊያን ወታደሮች ይማርኳቸው በነበሩ መሣሪያዎች ራሳቸውን እያደራጁ አብዛኛውን የገጠር ክፍል ተቆጣጠሩት።

ሁለተኛው የዓለም ጦርነት መቀስቀስ ለኢትዮጵያ ትልቅ ቦታ ነበረው። የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ሲቀሰቀስ ጣሊያን የናዚ ጀርመን አጋር ሆነች። ያን ጊዜ እንግሊዞች የጣሊያን ጠላት ሆነው ኢትዮጵያን መደገፍ ጀመሩ። ስለዚህም ወታደራዊ ድጋፍ ሰጥተው፤ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ወደ ኢትዮጵያ እንዲገቡ ረዷቸው። በጄኔራል ካኒንግሂም የሚመራው የእንግሊዝ ጦር ከኬንያ ተነስቶ ከደቡብ አቅጣጫ ወደ መሀል ኢትዮጵያ ሲገሰግስ፤ በጄኔራል ፕላት የሚመራው ጦር ከሱዳን ተነስቶ ወደ አሥመራ፤ ከዚያም ከሰሜን አቅጣጫ ወደ መሐል ኢትዮጵያ ተንቀሳቀሰ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የሚመራውና የአርበኞችና የእንግሊዝ አማካሪዎች የሚገኙበት ጌዲዮን ተብሎ የተሰየመው ጦር ከሱዳን ተነስቶ በኦሜድላ አልፎ በጐጃም በኩል ወደ መሐል ሀገር ገሠገሠ። በመካከለኛ ኢትዮጵያ አርበኞች በጣሊያን ወታደሮች ላይ ጥቃታቸውን አፋፋሙ። ጣሊያኖች ክፉኛ ተሸነፉ። በየቦታው ድል የመሆናቸው ዜና ናኘ። ዘመቻው ከተጀመረ ሁለት ወራት ሳይሞላው፤ ጣሊያኖች አዲስ አበባን ለቀው ፈረጠጡ። መጋቢት 28 ቀን 1933 ዓ.ም የጄኔራል ካኒንግሃም ጦር አዲስ አበባን ተቆጣጠረ። እንግሊዞች ኢትዮጵያውያን አርበኞች ወደ አዲስ አበባ እንዲገቡ ስላልፈለጉ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን በደብረ ማርቆስ ለአንድ ወር ያህል እንዲቆዩ አደረጓቸው።

ይሁንና በአዲስ አበባ በአርበኞች ተፅዕኖና ቅሬታ የተነሳ አርበኞች ወደ አዲስ አበባ እንዲገቡ ፈቀዱ። አፄ ኃይለ ሥላሴም ወደ አዲስ አበባ እንዲጓዙ ፈቀዱ። ንጉሠ ነገሥቱም አዲስ አበባ በታላቁ ቤተ መንግሥት የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ሰቀሉ። አጼ ኃይለሥላሴ አዲስ አበባ ገብተው የሚከተለውን ንግግር አድርገው ነበር።

‹‹ይህ የምትሰሙት ድምጽ የኔ የንጉሳችሁ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ነው። አባቶቻችን ደማቸውን አፍሰው አጥንታቸውን ከስክሰው በነፃነት ያቆዩልን ሀገራችንን ወደ ከፍተኛው የሥልጣኔ ደረጃ ለማራመድ የምንደክምበት ጊዜ ከጥንት ጀምሮ ስለሆነ ዳግመኛ ጠላታችን ኢጣሊያ ይህንን እይታ ወሰናችንን ጥሳ የግፍ ጦርነት እንዳደረገችብን ሁላችሁም የምታውቁት ነው።

እኛም በተቻለን ከተከላከልን በኋላ ርዳታ ለመጠየቅ ወደ መንግሥታት ማህበር ወደ ወዳጆቻችን መንግሥታቶች መጣን፤ እዚህ ስንነጋገር በቆየንበት ጊዜ የኢትዮጵያ አርበኞች ሰይፋችሁን ሳትከቱ ፊታችሁን ሳትመልሱ ሰንደቅ አላማችሁን ሳታጥፉ ለባዕድ አንገዛም በማለት በመሳሪያ ብዛት ከሚበልጣችሁ ጨካኝ ጠላት ጋር የባሕርይ የሆነውን ጀግንነታችሁን መሣሪያ አድርጋችሁ በኢትዮጵያ አምላክ ብቻ ተማምናችሁ በጀግንነት ቀንና ሌሊት በዱር በገደል ስትጋደሉ ቆይታችሁ ይኸው አሁን እንደምታዩት የማያቋርጥ የአምስት ዓመት ትግላችሁ የድካማችሁንና የመስዋዕታችሁን ፍሬ ለማየት እንድትበቁ አደረጋችሁ።

የሀገሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ! ዛሬ ኢትዮጵያ እጆቹዋን ወደ እግዚአብሔር ዘርግታ እልል እያለች ምስጋናዋን የምታቀርብበት ደስታዋንም ለልጆቹዋ የምትገልጽበት ቀን ነው። የኢትዮጵያ ልጆች ከባድ የመከራ ቀንበርና ከዘለዓለም ባርነት ነፃ የወጡበት ቀንና እኛም አምስት ዓመት ሙሉ ተለይተነው ከነበረው ከምንወደውና ከምንናፍቀው ሕዝባችን ጋር ለመቀላቀል የበቃንበት ቀን ስለሆነ ይህ ቀን የተከበረና የተቀደሰ በየዓመቱም ታላቁ የኢትዮጵያ በዓል የሚውልበት ነው። በዚህም ቀን ለሚዎዷት ለሀገራቸው ነፃነት ለንጉሠ ነገሥታቸውና ለሰንደቅ አላማቸወ ክብር አባቶቻቸው የተላለፈውን ጥብቅ አደራ አናስወስድም በማለት መስዋዕት ሆነው ደማቸውን ያፈሰሱትን አጥንታቸውን የከሰከሱትን ጀግኖቻችንን እናስታውሳለን። ለዚህም ለጀግኖቻችን የኢትዮጵያ ታሪክ ምስክር ይሆናል።›› አሉ፡፡

ንጉሡ ጨምረውም ‹‹ባለፈው አምስት ዓመታት ውስጥ በዝርዝር ተነግረውና ተቆጥረው የማያልቁ ያገኘናቸው መከራና ስቃይ ትምህርት ሆነውን ሠራተኛነት፣ አንድነት፣ ህብረትና ፍቅር በልባችሁ ተጽፈው ለምናስበው ለኢትዮጵያ ጉዳይ ረዳቶች ለመሆን ዋና ትምህርት የሚሰጣችሁ ነው። በአዲሷ ኢትዮጵያ ከእንግዲህ ወዲያ የማትነጣጠሉ በሕግ ፊት ትክክልና ነፃነት ያላችሁ ሕዝቦች እንድትሆኑ እንፈልጋለን። ሀገር የሚለማበትን ሕዝብ የሚበለጽግበትን እርሻ፣ ንግድ፣ ትምህርትና ጥበብ የሚስፋፉበትን የሕዝባችን ሕይወቱና ሀብቱ የሚጠበቅበትን የሀገር አስተዳደርም በአዲሱ ስልጣኔ ተለውጦ ፍጹም የሚሆንበትን ይህን ለመሰለው ለምንደክምበት ሥራ አብሮ ደካሚ መሆን አለባችሁ›› ብለው ነበር።

ይሄ የኢትዮጵያውያን የድል ብስራት የሆነው የአርበኞች ቀን ከፍተኛ ዋጋ የተከፈለበት ነው። በዚህ ጦርነት ውስጥ ምላጭ ስቦ ጥይት ከተኮሰው አርበኛ በተጨማሪ በየቤቱ ሆኖ በተለያየ መልክ በውጊያው የተሳተፈው ሰው ቀላል አልነበረም። በትግሉ ጊዜ የአርበኞች ዋናው ችግር ቀለብ ነበር። ቀለባቸውን የሚያገኙትም ከአርሶ አደሩ ቤት ነው። ይሄ ነገር የሚሆነው ታዲያ በግድም በውድም ነበር። በተለይም ከጠላት ጋር የሚያብሩ ሰዎችን ደግሞ እህላቸው እንዲዘረፍና ለሠራዊቱ ቀለብ እንዲሆን ተደርጓል።

ሠራዊቱ ‹‹ደረቅ ጦር›› እና ‹‹መደዴ ጦር›› ተብሎ ለሁለት ተከፍሎም ነበር። ደረቅ ጦር የተባለው ሙሉ በሙሉ ውጊያ ላይ የሚያተኩር ሲሆን፤ ‹‹መደዴ ጦር›› የተባለው ደግሞ እንደሁኔታው የእርሻ ሥራ ላይ እንዲሰማራ ይደረጋል። ነገሩ ሲከፋ ግን አርበኞች ፍራፍሬ፣ ቅጠላቅጠልና የዱር አውሬ ሁሉ እየበሉ ተዋግተዋል። እናቶች ከሠራዊቱ ጋር አብረው በመዝመት ምግብና ውሃ ከማቀበል በተጨማሪ ባህላዊ ሕክምና እየሰጡ ሠራዊቱን ታድገዋል። የወደቀውን በማንሳት የቆሰለውን በመጠገን ተሳትፈዋል። ይህ የአርበኞች ቀን የሁሉም ኢትዮጵያዊ የተጋድሎ ድል ነው ማለት ይቻላል።

በእዚህ የአርበኞች የድል በዓል ላይ የሲልቪያ ፓንክረስት አስተዋፅዖም ሊጠቀስ ይገባል። ሲልቪያ ፓንክረስት እንግሊዛዊት ናት። የኢትዮጵያ በፋሽስቶች መወረር ያንገበገባት ሴት ናት። ከኢትዮጵያ ንጉሠ ጎን በመቆም የኢትዮጵያ አርበኛ ሆነች። New Times and Ethiopian News የተሰኘ ጋዜጣ ማሳተም ጀመረች።

ጋዜጣው በየሳምንቱ ለእንግሊዝ ፓርላማ አባላት የሚበተን ነው። ቀሪው ደግሞ ለሌሎች ታላላቅ ሰዎች የሚሰጥ ነው። ጋዜጣው ኢትዮጵያ ውስጥ ፋሽስቶች እየፈፀሙ ስላሉት አሰቃቂ ግፍ የሚገልጽ ነው። እንደ እንግሊዝ ያሉ ታላላቅ መንግሥታት ይህን ግፍ እንዲቃወሙ የሚቀሰቅስ ነው። በመጨረሻም የእንግሊዝ መንግሥት ከኢትዮጵያ ጎን ቆሞ ፋሽስቶችን እንዲፋለም አደረገች።

አቶ ዘውዴ ረታ ደግሞ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት በሚለው መጽሐፋቸው ስለታሪካዊቷ ሚያዝያ 27 እንዲህ ጽፈዋል፦ ‹‹ሚያዝያ 27 ቀን 1933 ዓ.ም. ደግሞ ንጉሠ ነገሥቱ በከፍተኛ አጀብ እኩለ ቀን ስድስት ሰዓት ላይ ከታላቁ የዳግማዊ ምኒልክ ቤተ መንግሥት አደባባይ ላይ አረንጓዴ ቢጫ ቀዩን ሰንደቅ ዓላማችንን መልሰው ሰቀሉት፡፡ የክብር ዘብ ተሰልፎ፣ በራስ አበበ አረጋይ የሚመራው አሥር ሺህ አርበኞች ያሉት ጦር ዙሪያውን በሀገር ፍቅርና በብሔራዊ ስሜት እንደቆፈጠነ፣ በሱዳን በኩል የመጣውና በሻለቃ ዊንጌት የሚመራው የጌዲዮን ጦርም ተሰልፎ፣ መድፍ ተደጋግሞ እየተተኮሰ ሰንደቃችን በክብር ከፍ አለ፡፡›› ይላል፡፡

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ከስደት መልስ መናገሻ ከተማቸው ሚያዝያ 27 ቀን ገብተው የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ከማውለብለባቸው አራት ወር በፊት ጥር 12 ቀን ሱዳን ድንበርን ተሻግረው ኢትዮጵያ ገብተው ያውለበለቡት ኦሜድላ ላይ እንደነበር በመፅሐፉ ተጠቅሷል፡፡

ከሰማንያ ስምንት ዓመታት በፊት የተፈጸመው የፋሺስት ጣሊያን ወረራ በኢትዮጵያ ላይ ብዙ መከራዎችን ትቶ ማለፉ አይዘነጋም፡፡ አርበኞች ሀገራዊ ነፃነት ለማስከበር የሕዝቡን ልዕልና ለማስጠበቅ ያደረጉት ተጋድሎ የትየለሌ ነው፡፡ ጣሊያን በዓድዋ ላይ የደረሰበትን ሽንፈት ለመበቀል ከ40 ዓመት ቆይታ በኋላ በፋሺስታዊ መንግሥቷ አማካይነት በአምስቱ ዘመን የሠራችው ግፍ ተነግሮ አያልቅም፡፡ ወረራውን በፈጸመች ባመቱ በየካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም. በአዲስ አበባና በአካባቢው ከተፈጸመው ግፍ አንስቶ በሁሉም ክፍላተ ሀገር ብዙ ጥፋት ደርሷል፡፡

ከእነዚህም መካከል የመጀመሪያው የፋሺስት ወንጀለኞች የኢትዮጵያን ሠራዊት የፈቱበት በተምቤንና በሐሸንጌ በመርዝ ጋዘ ያደረሱት እልቂት ይጠቀሳል፡፡ ጣልያን ያልጠበቀችውና ዓለም አየዋለሁ ብላ ያላሰበችውን ድል ኢትዮጵያ በዓድዋ ተራሮች መካከል ተቀብላለች። ይህንንም ተከትሎ ሽንፈቷ የቆጫት የምትመስለው ጣልያን ቂም ይዛ ቆይታ፣ ለበቀል ከ40 ዓመታት በኋላ በ1928 ዳግም ኢትዮጵያን ወርራለች። ይህንንም በዘመናዊ የጦር መሣሪያና በወታደራዊ ኃይል ይበልጥ ተደራጅታ ያደረገችው በመሆኑ፣ በዓድዋ ጦርነት ከነበራት ትጥቅ ያልተሻለ ወታደራዊ አቅም ላልገነባችው ኢትዮጵያ እጅግ ከባድ ነበር። ነገር ግን አርበኞቿ በጽናት ከመዋጋት አልተቆጠቡምና ኢትዮጵያ ለማሸነፍ በቃች። ክብር ለሀገራቸው ደግም የማይተካ ውድ ሕይወታቸውን ያለስስት በመስጠት ነፃነቷን ጠብቃ እንድትኖር ለተዋደቁ ኢትዮጵያውያን!

# ስፖርት

## ሜይ ዴይ እና የሳባደሩ ስፖርት እንቅስቃሴ

ቦጋለ አበበ

ዛሬ ዓለም አቀፉ የሠራተኞች ቀን ሜይ ዴይ ነው፡፡ ይህ በዓል በሀገራችን ለ49ኛ በዓለም አቀፍ ደረጃ ደግሞ ለ135ኛ ጊዜ በተለያዩ ዝግጅቶች ተከብሮ ይውላል፡፡ የሠራተኛው ማህበረሰብ ሲነሳ ደግሞ በኢትዮጵያ ሠራተኛ ማህበራት ኮንፌዴሬሽን (ኢሰማኮ) አማካኝነት የሚካሄዱ የሠራተኞች የስፖርት ውድድሮች በአንጋፋነታቸው ብቻ ሳይሆን ባለፉት ዘመናት ለኢትዮጵያ ስፖርት ታላላቅ ስፖርተኞችን በማፍራት ትልቅ አስተዋፅኦ እንደነበራቸው መዘንጋት አይቻልም፡፡

የኢትዮጵያ ሠራተኞች የስፖርት ውድድር ዛሬም ቢሆን በሺዎች የሚቆጠሩ የሠራተኛ ማህበራትን በማሳተፍ ደማቅ የስፖርት መድረክ ሆነው ቀጥለዋል፡፡ ኢሰማኮ በየዓመቱ የበጋ ወራት ውድድሮች፣ የሜይ ዴይ መታሰቢያ ውድድሮችና ሀገር አቀፍ ውድድሮችን በየዓመቱ በማካሄድ ዘመናትን ተሻግሯል፡፡

የሠራተኞች የበጋ ወራት የስፖርት ውድድር ባለፈው ጥር 19-2016 በኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ ከተጀመረ ጀምሮም በደማቅ ሁኔታ መካሄዱን እንደቀጠለ የኢሰማኮ ማህበራዊ ጉዳይ መምሪያ ሃላፊና የስፖርት ኮሚቴ ሰብሳቢው አቶ ፍሰሃፂዮን ቢያድግልኝ ይናገራሉ። እንደ እሳቸው ገለፃ፣ የዘንድሮው ዓመት የሠራተኞች የበጋ ወራት ውድድሮች እግር ኳስና ቮሊቦልን ጨምሮ በተለያዩ የቤት ውስጥ ውድድሮች በጥሩ ሁኔታ እየተካሄደ ቀጥሏል። ኢሰማኮ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች እጥረት ቢኖርበትን የኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ፣ ዳግማዊ ምኒልክና ስብስቴ ነጋሲ ትምህርት ቤቶችና ሌሎችም ሊመሰገኑ የሚገባቸው ተቋማት የማዘውተሪያ ስፍራዎችን በመፍቀድ የሠራተኛው ስፖርት በድምቀት እየተካሄደ ይገኛል።

በዚህም ሠራተኞች በጥሩ የስፖርት ስሜት የእርስ በርስ ግንኙነታቸውን እያጠናከሩ ስፖርቱን ለጤና፣ ለወዳጅነትና ለምርታማነት ብሎም ለሰላም እየተጠቀሙት እንደሚገኙ ሃላፊው ያስረዳሉ፡፡ ሠራተኛው በሀገራችን ለ49ኛ በዓለም አቀፍ ደረጃ ደግሞ ለ135ኛ ጊዜ የሚከበረውን የሠራተኞች ቀን ሜይ ዴይን ዛሬ የሚያከብሩትም በዚህ ስሜት ነው። በዓሉ ሲከበርም የዘንድሮው መሪ ቃል «ለሰላምና ለኑሮ ውድነት መፍትሄ እንሻለን» በሚል ሃሳብ ነው። ይህን ምክንያት በማድረግም በዚህ ሳምንት የተለያዩ መርሃግብሮች እየተካሄዱ ይገኛሉ።



የሠራተኛው የበጋ ወራት ውድድሮች በተለያዩ የማዘውተሪያ ሥፍራዎች ጥሩ ፉክክር እያስተናገዱ ይገኛሉ፣

«ሠራተኛው ሰላምን አጥብቆ ይሻል፣ የኑሮ ውድነቱም እንዲቃለልለት መፍትሄ ይፈልጋልና በየስፖርት ሜዳውም ይሄን ድምፁን እያሰማ ይገኛል። ይሄንን ዓለም አቀፍ የሰራተኞች ቀን ሜይ ዴይ መታሰቢያ ስናከብር ሠራተኛውም አሰሪውም አጥብቆ ለሚፈልገው ሰላም መትጋት አለበት፣ መንግሥትም የኑሮ ውድነቱ እንዲቃለል የበለጠ ጥረት እንዲያደርግ፣ ምርትና ምርታማነትን ለማረጋገጥ በቅድሚያ ሰላም ለማስፈን ጥረት ማድረጉን መቀጠል አለበት። በዚህ አጋጣሚ መንግሥትና ሠራተኛው በመወያየት እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ መሥራት ተገቢ ይሆናል። ባለፈው ነሐሴ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) ከኢሠማኮ ሥራ አስፈፃሚ ጋር ውይይት አድርገው ነበር፡፡ ከዚህ በኋላም ከሠራተኛው ጋርም የሚነጋገሩበት እድል እንደሚኖር እናምናለን፡፡» በማለት አቶ ፍሰሃፂዮን ገልፀዋል፡፡

ስፖርት ለሰላም፣ ለወዳጅነትና ለምርትማነት እንደመሆኑ ሠራተኛውም ስፖርቱን በእነዚህን መርሆች መሠረት በተለያዩ ክልሎች ቅርናጫፍ ፅህፈት ቤቶች እያካሄዱ ይገኛል፡፡ በሀገር አቀፍ ደረጃ ሜይ ዴይን በተመለከተ የሚካሄዱ ውድድሮችን በአንድ ላይ በማካሄድ ለማክበር አሁን ላይ በአንዳንድ አካባቢዎች ባሉ የፀጥታ ስጋቶች አልተቻለም፡፡ ወደፊት ግን ይህ ስጋት ሲቀረፍ የሜይ ዴይ ውድድሮች የሚቀጥሉ ይሆናል፡፡ የሜይ ዴይን የጥሎ ማለፍ ውድድሮች ዘንድሮ ባህርዳር ነበር ለማክበር የታሰበው፣ ይሁን እንጂ ከፀጥታ ስጋት ጋር በተያያዘ ማካሄድ አልተቻለም። ወደፊት ግን የሰላሙ ሁኔታ ሲስተካከል ውድድሩም እንደሚመለስ አቶ ፍሰሃፂዮን ይናገራሉ፡፡ እስከዚያው ግን ሠራተኛው ሳምንቱን በበጋ ወራት ውድድሮች ቀኑን በድምቀት እያከበረ ይገኛል፡፡

የኢሰማኮ የስፖርት ክፍል ሃላፊው አቶ ዮሴፍ ካሳ በበኩላቸው፣ የዘንድሮው የበጋ ወራት ውድድር ከተጠበቀው በላይ በድምቀት መካሄዱን እንደቀጠለ ያስረዳሉ፡፡ በአስር የስፖርት አይነቶች በርካታ የሠራተኛ ማህበራት የስፖርት ቡድኖችም የነቃ ተሳትፎ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ ቀደም ባሉት ዓመታት በዓመት ሦስት የሠራተኛው የውድድር መድረኮች የሚካሄዱ ቢሆንም ከበጀት እጥረትና ከሌሎች ችግሮች ጋር በተያያዘ ዘንድሮ የሜይ ዴይን ውድድር ማድረግ አልተቻለም። ለረጅም ጊዜ የሚቆዩት የበጋ ወራት ውድድሮች ግን በተለያዩ የማዘውተሪያ ሥፍራዎች ጥሩ ፉክክር እያስተናገዱ ይገኛሉ፡፡ እንደ አቶ ዮሴፍ ማብራሪያ፣ ቀደም ሲል በጥሎ ማለፍ ውድድር የሜይ ዴይ ፉክክሮች ይካሄዱ ነበር፣ ዘንድሮ ይህን ማድረግ ባይቻልም የበጋ ወራት ውድድሮች አጠቃላይ ድባብ ያንን እንዲተኩ አድርገዋል፡፡ ባህርዳር፣ አዳማ፣ መቀሌ፣ሐዋሳና ጅማ የኢሠማኮ የተለያዩ ቅርናጫፍ ፅህፈት ቤቶች ባሉበት የሜይ ዴይ ውድድሮች በየዓመቱ ሲካሄዱ ሠራተኞች ወደ ተለያዩ አካባቢዎች በመሄድ እርስበርስ የሚገናኙበትና ተጨማሪ የውድድር አማራጭም የሚያገኙበት ነው፡፡ ይህም በቀጣይ ዓመታት አሁን ያሉ ችግሮችና የፀጥታ ስጋቶች ሲቀረፉ ውድድሩም እንደሚመለስ ተስፋ አላቸው፡፡

ከሠራተኛው ባሻገር አሰሪዎችም ሠራተኞቻቸውን ወደ ስፖርቱ በመላክ ጥሩ ለውጥ እያሳዩ እንደሚገኙ የጠቆሙት አቶ ዮሴፍ፣ የስፖርት መድረኩ ራሳቸውን የሚያስተዋውቁበት በመሆኑም እድሉን እየተጠቀሙበት እንደሚገኙ አስረድተዋል።


## የጨረታ ማስታወቂያ ጨረታ ቁጥር -22/2016 ዓ.ም

በጉምሩክ ኮሚሽን የኮምቦልቻ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በተለያዩ ጊዜ ውርስ የተደረጉ ኤሌክትሮኒክስ ከረሜላ፣ መዳብ እና ጫማ በግልፅ ጨረታ እንዲሁም ፕላንፕሌት፣Sythetic Pigment (አይረን ኦክሳይድ) ፣የቲማቲም ማቀነባበሪያ ማሽን የወጥ ቤት ዕቃ፣ መለዋወጫ እና የኮስሞቲክስ ዕቃዎች በሀራጅ ጨረታ ባሉበት ሁኔታ መሸጥ ይፈልጋል፡

በመሆኑም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የተጫራቾች መመሪያ የምታሟሉ ተጫራቾች መወዳደር የምትችሉ ሲሆን መስፈርቶቹ፡-

1. በጨረታው ለመወዳደር የሚፈልግ ማንኛውም ተጫራች በጨረታ ከሚሸጠው ዕቃ ጋር ተዛማጅነት ያለው የፀና ንግድ ፈቃድ፣ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ምዝገባ ሰርተፍኬት እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ማቅረብ የሚችል ግለሰብ መጫረት ይችላል፡፡
2. የዚህ አንቀፅ ተራ ቁጥር (1) ድንጋጌ ቢኖርም ግምታዊ ዋጋው ከብር 500 ሽህ በታች የሆነ ማንኛውንም ዕቃ ለመግዛት የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ የምስክር ወረቀት (ሰርትፍኬት) ማቅረብ አያስፈልገውም፡፡
3. በተጠቀሰው መስፈርት በጨረታ የሚሸጠው እቃ በኮሚሽኑ ቁጥጥር ስር ከመግባቱ በፊት ባለቤት የነበረ ወይም የባለቤቱ ወኪል ወይም ቤተሰብ የሆነ ሰው በማንኛውም መልኩ በጨረታው መሳተፍ አይችልም፡፡
4. ተጫራቾች የዕቃዎቹን ዝርዝር፤ አይነትና ብዛት የጨረታ ሰነድና መመሪያ እንዲሁም የጨረታ ዋጋ ማቅረቢያ ቅፅ የማይመለስ ብር 100 (አንድ መቶ) እየከፈሉ ኮምቦልቻ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የጉምሩክ ሂሳብ ቡድን ማስታወቂያው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ ስምንተኛው (8) ቀን 03፡00 ሰዓት ድረስ መግዛት ይችላሉ፡፡
5. ተጫራቾች ለጨረታው የዕቃዎችን ዝርዝር በያዘው ሰነድ ላይ ተጫራቹ የሰጠው ዋጋ በሚለው አምድ ሥር የሚገዙበትን ዋጋ በአሀዝና በፊደል ገልፀው በኢንቬሎፕ ወይም በፖስታ በማሸግ ጉምሩክ ኮሚሽን ኮምቦልቻ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በዉርስ መጋዘን የስራ ሂደት ቢሮ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስታወቂያው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ ስምንተኛው ቀን 3፡50 ሰዓት ድረስ ማስገባት አለባቸው።
6. የጨረታ ማስታወቂያው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት በስምንተኛው ቀን በጉምሩክ ኮሚሽን ኮምቦልቻ ቅ/ፅ/ቤት በውርስ መጋዘን ቢሮ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት የሚካሄድ ሲሆን ግልፅ ጨረታዉ 3፡50 ሰዓት ተዘግቶ 4፡00 ሰዓት የሚከፈት ሲሆን ሀራጅ ጨረታው 4፡45 ሰዓት የሚጀመር ይሆናል፡፡
7. ተጫራቾች በጨረታው አሸናፊ መሆናቸው ከተገለፀበት ቀን ጀምሮ በ-05-ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ ያሸነፉበት ዋጋ በመክፈል ንብረቶቹን ማንሳት ይኖርባቸዋል፡፡ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ከፍለው የማይወስዱ ተጫራቾች ያስያዘ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና (CPO) ለመ/ቤቱ ገቢ ተደርጎ እቃው እንደገና ለጨረታ ይቀርባል፡፡
8. ተጫራቾች ለእቃዎች በሚያቀርቡት የመጫረቻ ዋጋ አሸናፊ ከሆኑ ተጨማሪ ዕሴት ታክስ 15% (VAT) የሚጨመርበት ይሆናል፡፡
9. ተጫራቾች ጨረታው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ ሰባተኛዉ ቀን ድረስ ለሽያጭ የተዘጋጁ እቃዎችን በኮምቦልቻ ጉምሩክ ቅ/ፅ/ቤት በውርስ መጋዘን ቢሮ (አዲስ በሚሰራው የጉምሩክ ህንፃ) በስራ ሰዓት ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት እስከ 6፡00 ሰዓት ከሰዓት በኋላ ከ8፡00 ሰዓት እስከ 10፡00 ሰዓት ድረስ እና በስምንተኛው ቀን ጧት 3፡00 ሰዓት ድረስ መመልከት ይችላሉ፡፡
10. ተጫራቾች ለግልፅ ጨረታ እቃዎች የሰጡትን የመግዣ ዋጋ አምስት በመቶ (5%) እና ለሀራጅ ጨረታ እቃዎች ሀምሳ ሽህ (50,000) ብር የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና በባንክ የተረጋገጠ ሲፒኦ (CPO) ከዋጋ ማቅረቢያ ቅፅ ጋር ማቅረብ አለባቸው፡፡
11. መስሪያ ቤቱ ጨረታውን በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

ለተጨማሪ ማብራሪያ በስልክ ቁጥር 033 551 06 93 ደውለው መጠየቅ ይችላሉ፡

**ጉምሩክ ኮሚሽን ኮምቦልቻ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት**